# ክርስቶስ ድል ነሣ

- እርኩሳን መናፍስት በታላቅ ድል ተመትተዋል!
- አታላዩን ሰይጣንና አጋንንትን አታምልኩ።
- ለመግዛትና ለመሸጥ እንዲችሉ ብለው የአውሬውን ምልክት በእጃቸውና በግንባራቸው ላይ የተቀበሉ ሁሉ ይጠፋሉ።

በዋትሰን ጉድማን የተቀነባበሩ
የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች

የማይሸጥ በነፃ የሚታደል

# ክርስቶስ ድል ነሣ

በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ «የዚህ ዓለም ገዢ» የተባለው ሰይጣን ቀንደኛው የእግዚአብሔርና ታላቁ የእግዚአብሔር ፍጡር የሆነው የሰው ልጅ ጠላት ነው። እኛም የሰው ልጆች ከባድ በሆነ ጦር ሜዳ ላይ እንገኛለን። ጦርነቱም የሚካሄደው በሰይጣንና በክርስቶስ መካከል ነው። እኛም ከሁለቱ መካከል የዘለዓለም መፈያችን የሚሆነውን የዓለም ፈጣሪ የሆነውን ክርስቶስን — ማለት ከእኛ ጋር የሆነውን አምላክ — አማኑኤልን ወይም የእግዚአብሔር ተቃዋሚ የሆኑት ነገሮች ሁሉ ገዢ የሆነውን ሰይጣንን በማለትን መምረጥ ይኖርብናል። ክርስቶስ በሞቱና በትንሣኤው በእውነት ለሚያምኑበት ሁሉ ፍጹም የሆነ ድል አድርጎላቸዋል።

ሰይጣን በተለያዩ ብዙ መንገዶች ሰዎችን ለማሳሳትና ባልሆነ መንገድ ለመምራት ይሞክራል። ሰው እንዲያመልከው ለማድረግ ይፍጨረጨራል። አምልኮና ስግደት ሁሉ የሚገባው ግን ፈጣሪያችን ለሆነው ለክርስቶስ ብቻ ነው። እኛም ተለይተን የምንታወቀው በምናመልከው ነገር እንጻር ነው። ሰይጣንም የዓለምን ሰዎች ሁሉ ለመያዝ የሚሞክርባቸው ዘዴዎች የሚከተሉት ናቸው፡— 1. በእግዚአብሔር እንዳይታመኑ ያገፋፋቸዋል፤ 2. ለአጋንንት እንዲታዘዙ ያበረታታቸዋል፤ 3. «የኃጢአት ሰው» ተብሎ የተጠራውን የጥፋት ልጅ እንዲያመልኩ ይመራቸዋል፤ 4. ለምስሉ እንዲሰግዱ ያነቃቃቸዋል፤ 5. ንግዳቸው እንዲስፋፋ የርሱን ዘዴና ምልክት እንዲቀበሉ ይመክራቸዋል። ከእነዚህ ሁሉ ተጠንቀቁ!

# የሰይጣንን ዐመጽ ምን አስነሣው ?



ምሳሌ : 16 ÷ 18

ትዕቢት ፡ ጥፋትን ፡ ዅሩ ፡ መንፈስም ፡ ውድቀትን ፡ ይቀድማል ።

ሕዝቅኤል ፡ 28 ÷ 17-19

በውበትህ ፡ ምክንያት ፡ ልብህ ፡ ኰርቶአል ፤ ከክብርህ ፡ የተነሣ ፡ ጥበብ ህን ፡ አረከስህ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ጣልሁህ ፡ ያዩ ህም ፡ ዘንድ ፡ በነገሥታት ፡ ፊት ፡ ሰጠሁህ ።

## የአመጸኛው መድረሻ

በበደልህ ፡ ብዛት ፡ በንግድህም ፡ ኃጢአት ፡ መቅደስህን ፡ አረከስህ ፡ ስለዚህ ፡ እሳትን ፡ ከው ስጥህ ፡ አውጥቻለሁ ፡ እርስዋም ፡ በልታሃለች ÷ በሚያዩህም ፡ ሁሉ ፡ ፊት ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ አመድ ፡ አድርጌሃለሁ ። በአሕዛብም ፡ ውስጥ ፡ የሚያውቁህ ፡ ሁሉ ፡ ይደነቁብሃል ፡ አንተም ፡ ለድ ንጋጤ ፡ ሆነሃል ÷ እስከ ፡ ዘላለምም ፡ አትገኝም ።

## ማንኛውም ፍጡር ለፈጣሪው መገዛት አለበት

መዝሙረ ፡ ዳ ዊ ት ፡ 100 ÷ 2-3

በደስታም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ተገዙ ÷
በሐሤትም ፡ ወደ ፡ ፊቱ ፡ ግቡ ።
እግዚአብሔር ፡ እርሱ ፡ አምላክ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እወቁ ፡
እርሱ ፡ ሠራን ፡ እኛም ፡ አይደለንም ፡
እኛስ ፡ ሕዝቡ ፡ የማሰማርያውም ፡ በጎች ፡ ነን ።

# ሰይጣን ያወጀው ዐመጸኛነት

## ፈቃዱ እግዚአብሔርን ይቃረናል

ኢሳይያስ 14 ÷ 12-19

አንተ፡የንጋት፡ልጅ፡አጥቢያ፡ኮከብ፡ሆይ÷ እንዴት፡ከሰማይ፡ወደቅህ! አሕዛብንም፡ያዋ ረድህ፡አንተ፡ሆይ÷እንዴት፡እስከ፡ምድር፡ ድረስ፡ተቈረጥህ! አንተም፡በልብህ፡— ወደ፡ ሰማይ፡ ዐርጋለሁ÷ ዙፋኔንም፡ ከእግዚአብ ሔር፡ከዋክብት፡በላይ፡ከፍ፡ከፍ፡አደርጋለሁ÷ በሰሜንም፡ዳርቻ፡በመሰብሰቢያ፡ተራራ፡ ላይ፡እቀመጣለሁ፤ ከዳመናዎች፡ከፍታ፡ በላይ፡ ዐርጋለሁ÷ በልዑልም፡እመሰላለሁ፡ አልህ ።

## በምድር ላይ ጥፋት ይሠራጫል

ነገር፡ግን፡ወደ፡ሲኦል፡ወደ፡ጕድ ጓዱም፡ጥልቅ፡ትወርዳለህ ። የሚያዩህ፡ይመ ለከቱሃልና፡— በውኑ፡ምድርን፡ያንቀጠቀጠ፡ መንግሥታትንም፡ያናወጠ÷ዓለሙን፡በድማ፡ ያደረገ÷ ከተሞችንም፡ያፈረሰ÷ ምርኮኞቹ ንም፡ወደ፡ቤታቸው፡ያልሰደደ፡ሰው፡ይህ፡ ነውን? ብለው፡ያስተውሉሃል ።

## በእግዚአብሔር ዘንድ አጸያፊ ነው

የአሕዛብ፡ነገሥታት፡ሁሉ፡በየቤታቸው፡ በክብር፡ አን ቀላፍተዋል ። አንተ፡ግን፡ እንደ፡ ተጠላ፡ ቅርንጫፍ፡ ከመቃብርህ፡ ተጥለሃል ።

# በእግዚአብሔር ላይ ማመጽ ያስቀጣል

## ሰይጣን ይቀጣል

ሉቃስ፡10÷18

እንዲሁም፡ አላቸው፡ ሰይ ጣንን፡ እንደ፡ መብረቅ፡ ከሰማይ፡ ሲወድቅ፡ አየሁ ።

## የተከተሉት መላእክት ይቀጣሉ

2 ጴጥሮስ፡2÷4

እግዚአብሔር፡ ኃጢአትን፡ ላደረጉ፡ መላእክት፡ ሳይራራላቸው፡ ወደ፡ ገሃነም፡ ጥሎ፡ በጨለማ፡ ጉድጓድ፡ ለፍርድ፡ ሊጠበቁ፡ አሳልፎ፡ ከሰጣቸው ፥

## የተታለሉት ሰዎች ይቀጣሉ

1 ጢሞቴዎስ፤3÷6

በትዕቢተ፡ ተነፍቶ፡ በዲያብሎስ፡ ፍርድ፡ እንዳይወድቅ፡ አዲስ፡ክርስቲያን፡አይሁን ።

## ሰይጣን በሰዎች ላይ ይሰለጥናል

2 ጴጥሮስ፡2÷19

ሰው፡ለተሸነፈበት፡ለእርሱ፡ተገዝቶ፡ባሪያ፡ነውና ።

## በመንግሥተ ሰማያት አንድ ገዢ ብቻ መኖር ይገባዋል ። ይኸውም፥— እግዚአብሔር ነው ።

ሮሜ፡12÷2

የእግዚአብሔር፡ፈቃደ. እርሱም፡ በጎና፡ ደስ፡ የሚያሰኝ፡ ፍጹምም፡ የሆነው፡ነገር፡ ምን፡ እንደ፡ ሆነ፡ ፈትናችሁ፡ ታውቁ፡ዘንድ፡ በልባችሁ፡መታደስ፡ተለወጡ፡ እንጂ፡ ይህን፡ ዓለም፡ አትምሰሉ ።

# አምልኮ ለእግዚአብሔር ብቻ ተገቢ ነው

ዘዳግም፡ 5 ÷ 6 – 7

እኔ ፡ የእግዚአ ብሔርን ፡ ቃል ፡ እነግራችሁ ፡ ዘንድ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ በእግዚአብሔርና ፡ በእናንተ ፡ መካከል ፡ ቆሚ ፡ ነበር ፡ እናንተ ፡ በእሳቱ ፡ ምክንያት ፡ ፈርታችኋልና ÷ ወደ ፡ ተራራውም ፡ አልወጣ ችሁምና ። እርሱም ፡ አለ ፡—

ከግብፅ ፡ ምድር ፡ ከባርነት ፡ ቤት ፡ ያወጣ ሁህ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክህ ፡ እኔ ፡ ነኝ ።

ከእኔ ፡ በቀር ፡ ሌሎች ፡ አማልክት ፡ አይሁኑ ልህ ።

የዮሐንስ ፡ ራእይ 19 ÷ 10

ልሰግድለትም ፡ በእግሩ ፡ ፊት ፡ ተደፋሁ ። እርሱም ፡ እንዳታደርገው ፡ ተጠንቀቅ ፡ ከአንተ ፡ ጋር ፡ የኢየሱስም ፡ ምስ ክር ፡ ካላቸው ፡ ከወንድሞችህ ፡ ጋር ፡ አብሬ ፡ ባሪያ ፡ ነኝ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ስገድ ።

መዝሙረ ፡ ዳዊት፡ 95 ÷ 6

ኑ ፡ እንስገድ ፡ ለእርሱም ፡ እንገዛ ፡ በእርሱ ፡ ባደረገን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት እን በርከክ ፡

እርሱ ፡ አምላካችን ፡ ነውና

እኛ ፡ የማሰማርያው ፡ ሕዝብ ፡ የእጁም ፡ በጎች ነንና ።

## የተታለሉትም አመጻኛውን ያመልካሉ

የዮሐንስ ፡ ራእይ፤ 13 ÷ 3-4

ምድርም ፡ ሁሉ ፡ አውሬውን ፡ እየተከተለ ፡ ተደነቀ ለዘንዶውም ፡ ስገዱለት ÷ ለአውሬው ፡ ሥልጣንን ፡ ሰጥቶተ ልና ።

## ሰይጣንና አጋንንት አምል ኮውን በጣም ይቋምጣሉ

ማቴዎስ፡ 4 ÷ 8 - 9

ደግሞ፡ዲያብሎስ፡እጅግ፡ረጅም፡ወደ፡ሆነ፡ተራራ፡ወሰደው፡የዓለምንም፡መንግሥታት፡ሁሉ፡ክብራቸውንም፡አሳይቶ፡— ወድቀህ፡ብትሰግድልኝ፡ይህን፡ሁሉ፡እሰጥሃለሁ፡አለው።

የዮሐንስ፡ራእይ ፡ 9 ÷ 20

በእነዚህም፡መቅሠፍቶች፡ያልተገደሉት፡የቀሩቱ፡ሰዎች፡ለአጋንንትና፡ያዩ፡ወይም፡ይሰሙ፡ወይም፡ይሄዱ፡ዘንድ፡ለማይችሉ፡ከወርቅና፡ከብር፡ከናስም፡ከድንጋይም፡ከእ ንጨትም፡ለተሠሩ፡ለጣዖቶች፡እንዳይሰግዱ፡ስለ፡እጃቸው፡ሥራ፡ንስሐ፡አልገቡም።

## እግዚአብሔር እነዚህን ያጠፉቸዋል

የዮሐንስ፡ራእይ፡16÷2 ፣ 20÷13 - 14

የአውሬውም ፡ ምልክት ፡ ባለባቸው ለምስሉም፡በሚሰግዱ፡ሰዎች፡ክፉኛ፡የሚነ ዘንዝ፡ቍስል፡ሆነባቸው።

እያንዳንዱም፡እንደ፡ሥራው፡መጠን፡ተከፈለ። ሞትና፡ሲኦልም፡በእሳት፡ባሕር፡ውስጥ፡ተጣሉ። ይህም፡የእሳት፡ባሕር፡ሁለ ተኛው፡ሞት፡ነው።

ኢሳይያስ፡ 42÷8

እኔ፡እግዚአብሔር፡ነኝ፡ስሜ፡ይህ፡ነው፡ክብ ሬን፡ለሌላ÷ምስጋናዬንም፡ለተቀረጹ፡ምስ ሎች፡አልሰጥም።

## የጌታ መላእክት ከሰይጣን መላእክት ይልቅ ብርቱዎች ናቸው

መዝሙረ ፡ ዳዊት ፡ 103÷20

ቃሉን፡የምትፈጽሙ ÷ ብርቱዎችና፡ኃያላን÷ የቃሉንም ፡ ድምፅ ፡ የምትሰሙ ፡ መላእክቱ ፡ ሁሉ ÷ እግዚአብሔርን፡ባርኩ ።

የዮሐንስ፡ራእይ ፡12÷ 7-8

በሰማይም ፡ ሰልፍ ፡ ሆነ ፡ ሚካኤልና ፡ መላ እክቱ፡ዘንዶውን፡ተዋጉ ። ዘንዶውም ፡ ከመ ላእክቱ፡ ጋር፡ተዋጋ፡ አልቻላቸውምም÷

## የእግዚአብሔር መላእክት የ ጌታን ሰዎች ያገለግሉአቸዋል ይጠብቁአቸውማል

ዕብራውያን ፡1÷14

ሁሉ ፡ መዳንን፡ ይወ ርሱ ፡ ዘንድ ፡ ስላላቸው ፡ ለማገዝ ፡ የሚላኩ ፡ የሚያገለግሉም፡ መናፍስት፡ አይደሉምን ?

ሉቃስ ፡11÷26

ከእርሱ ፡ የከፉትን ፡ ሌሎችን ፡ ሰባት፡ አጋንንት ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ይይዛል ÷

1 ጢሞቴዎስ፡4÷1

መንፈስ፡ግን፡በግልጥ ፡— በኋለኞች፡ዘመ ናት፡አንዳንዶች፡የሚያስቱ ፡ መናፍስትንና፡ በውሸተኞች፡ግብዝነት፡የተሰጠውን፡የአጋን ንትን ፡ ትምህርት ፡ እያደመጡ ፡ ሃይማኖትን ፡ ይክዳሉ፡ይላል ።

## በፈጣሪው መልክ የተፈጠረውን

ሲቀርብም፡ጋኔኑ፡ጣለ ውና፡አንፈራገጠው፡ ኢየሱስ፡ ግን፡ ርኩሱን፡ መንፈስ ፡ ገሥጸ፡ ብላቴናውን፡ፈወሰው፡ለአ ባቱም፡መለሰው ።
— ሉቃስ 9÷42

## የእግዚአብሔር በረከት የሆ ኑትን ቤተሰቦችን

የሚባርኩህንም ፡ እባርካለሁ ÷ የሚረግሙህ ንም፡እረግማለሁ ፤ የምድር፡ነገዶችም፡ሁሉ፡ በአንተ ፡ ይባረካሉ ። — ዘፍጥረት፡12÷3

## ደኅንነትን በማንነቱና በደሙ የሚያከናውነውን በሥጋ የተ ገለጸ አምላክ ክርስቶስን

ከዚህ፡በኋላ፡ሄሮድስ፡ሰብአ፡ሰገል፡እንደ ተሣለቁበት ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ ተቈጣና ፡ ልኮ፡ከሰብአ፡ሰገል፡እንደ ተረዳው፡ዘመን፡ በቤተ፡ ልሔምና፡ በአውራጃዋ፡ የነበሩትን፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ የሆናቸውን፡ከዚያም፡ የሚያ ንሱትን፡ሕፃናትን፡ሁሉ፡አስገደለ ።
— ማቴዎስ ፡ 2÷16

## ስለሚቃረነው የእግዚአብሔ ርን ቃል

ሴቲቱንም ፡ — በውኑ፡እግዚአብሔር፡ከገነት፡ ዛፍ፡ሁሉ፡እንዳትበሉ፡አዝዞአልን ? አላት ። ሴቲቱም፡ለእባቡ፡አለችው፡— በገነት፡ካለው፡ ከዛፍ ፡ ፍሬ፡ እንበ ላለን፡ነገር፡ግን፡በገነት፡ መካከል፡ካለው፡ ከዛፉ፡ፍሬ÷እግዚአብሔር፡ አለ ፡ እንዳት ሞቱ ፡ ከእርሱ ፡ አትብሉ፡ አትንኩትም ። እባ ብም፡ለሴቲቱ፡ አላት፡— ሞትን፡አትሞቱም ። — ዘፍጥረት ፡ 3÷1-4

## የበለቤትነትን ምልክት

የዮሐንስ ፡ ራእይ ፡ 22 ÷ 3 - 4

ከእንግዲህም ፡ ወዲህ ፡ መርገም ፡ ከቶ ፡ አይሆንም ። የእግዚአብሔርና ፡ የበጉም ፡ ዙፋን ፡ በእርስዋ ፡ ውስጥ ፡ ይሆናል ፥ ባሪያዎቹም ፡ ያመልኩታል ፡ ፊቱንም ፡ ያያሉ ፥ ስሙም ፡ በግምባሮቻቸው ፡ ይሆናል ።

## ወንጌልን በውሸት ያጣምመዋል

ገላትያ ፡ 1 ÷ 6 — 7

በክርስቶስ ፡ ጸጋ ፡ እናንተን ፡ ከጠራችሁ ፡ ከእ ርሱ ፡ ወደ ፡ ልዩ ፡ ወንጌል ፡ እንዲህ ፡ ፈጥናችሁ ፡ እንዴት ፡ እንዳለፋችሁ ፡ እደነቃለሁ ፡ እርሱ ፡ ግን ፡ ሌላ ፡ ወንጌል ፡ አይደለም ፤ የሚያናውጡ አችሁ ፡ የክርስቶስንም ፡ ወንጌል ፡ ሊያጣምሙ ፡ የሚወዱ ፡ አንዳንዶች ፡ አሉ ፡ እንጂ ።

## የእግዚአብሔርን አገልጋዮች በመምሰል ይቀርባል

2 ቆሮንቶስ ፡ 11 ÷ 13 - 14

እንደ ፡ እነዚህ ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ የክርስቶስን ፡ ሐዋ ርያት ፡ እንዲመስሉ ፡ ራሳቸውን ፡ እየለወጡ ፥ ውሸተኞች ፡ ሐዋርያትና ፡ ተንኰለኞች ፡ ሠራ ተኞች ፡ ናቸውና ። ይህም ፡ ድንቅ ፡ አይደለም ፡ ሰይጣን ፡ ራሱ ፡ የብርሃንን ፡ መልአክ ፡ እንዲመ ስል ፡ ራሱን ፡ ይለውጣልና ።

## የእግዚአብሔር ተአምራትና የኃሰተኛው ድንቆች ተነጻጽረ ዋል

1 ዮሐንስ፡ 5÷21

ልጆች፡ሆይ ከጣዖታት ፡ ራሳችሁን ፡ ጠብቁ።

ዘጸአት፡ 20÷3 - 5

ከእኔ ፡ በቀር፡ ሌሎች ፡ አማልክት ፡ አይሁ ኑልህ ።

በላይ፡ በሰማይ ፡ ካለው ÷ በታችም ፡ በም ድር ፡ ካለው ÷ ከምድርም ፡ በታች ፡ በውኃ፡ ካለው ፡ ነገር፡ የማናቸውንም ፡ ምሳሌ ፡ የተቀረ ጸውንም፡ ምስል ፡ ለአንተ፡ አታድርግ ። አትስ ገድላቸው ፡ አታምልካቸውምም ።

## ለሌሎቹ አማልክት አትስ ገዱ ፣ በእግዚአብሔር ፊት አ ስጸያፊዎች ናቸው

ዘዳግም ፡ 12÷2 ፡ 30 - 31

እናንተ ፡ የምትወርሱአትው ፡ አሕዛብ ፡ አማልክቶቻቸውን ፡ ያመለኩባቸውን ፡ በረጅም ፡ ተራሮች፡ በኮረብቶችም ፡ላይ፡ ከለም ለምም ፡ ዛፍ ፡ በታች ፡ ያለውን ፡ስፍራ ፡ ሁሉ ፡ ፈጽማችሁ አጥፉአቸው !

በምድራቸውም ፡ በተቀመጥህ፡ ጊዜ ÷ ከፊትህ፡ ከጠፉ ፡ በኋላ ፡ እነርሱን ፡ ለመከተል ፡ እንዳት ጠመድ ፡ እግ ዚአብሔር ፡ የሚጠላውን ፡ ርኵሰት ፡ ሁሉ ፡ እነ ርሱ ፡ ለአማልክቶቻቸው ፡ አድርገዋልና ÷ ወን ዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆቻቸውን ፡ ደግሞ ፡ ለአማ ልክቶቻቸው ፡ በእሳት ፡ ያቃጥሉአቸዋልና ፡ አንተ ፡ ለአምላክህ፡ ለእግዚአብሔር፡ እንዲሁ፡ አታድርግ ።

የሆዴ ንም ፡ ፍሬ ፡ ስለ ፡ ነፍሴ ፡ ኃጢአት፡ እሰጣለሁን ? — ሚ ክ ያ ስ ፡ 6÷7

## የክርስቶስ ደም (ሞቱ) ኃጢ አትን አጥቦ ያስወግዳል

## ጣዖትን የማምለክ ምኝነት

ይህም፡ የእግዚአብሔርን፡እውነት፡በውሸት፡ስለ፡ለወጡ፡በፈጣሪም፡ፈንታ፡የተፈጠረውን፡ ስላመለኩና፡ስላገለገሉ፡ነው፡እርሱም፡ለዘላለም፡የተባረከ፡ነው፡አሜን ። — ሮሜ፡1÷25

መዝሙረ ፡ ዳዊት፡115÷3 - 8

አምላካችንስ፡በላይ፡በሰማይ፡ነው፤
በሰማይም ፡ በምድርም፡
የፈቀደውን፡ሁሉ፡አደረገ።
የአሕዛብ፡ጣዖታቶች፡የወርቅና፡የብር÷
የሰው፡እጅ፡ሥራ፡ናቸው።
አፍ፡አላቸው፡አይናገሩምም፤
ዓይን፡አላቸው፡አያዩምም፤
ጆሮ፡አላቸው፡አይሰሙምም፤
አፍንጫ፡አላቸው፡አያሸትቱምም፤
እጅ፡አላቸው፡አይዳስሱምም፤
እግር፡አላቸው፡አይሄዱምም፤
በጉሮሮአቸውም፡አይናገሩም።
የሚሠሩአቸውም፡
የሚያምኑባቸውም፡ሁሉ፡እንደ፡እነርሱ፡
ይሁኑ።

## ጣዖትን ማምለክ ዲያብሎስን ማምለክ ነው

ቆሮንቶስ፡10÷14፦20

ጣዖትን፡ከማምለክ፡ሽሹ። . . . . . . . . — . . . . ___ ___ ______ ___ ___ አይደለም ፡ ነገር ፡ ግን፡አሕዛብ፡የሚሠዉት፡ለአጋንንት፡እንዲሆን፡እንጂ፡ለእግዚአብሔር፡እንዳይሠዉ፡እላለሁ ፡ ከአጋንንትም ፡ ጋር፡ማኅበረተኞች፡እንድትሆኑ፡አልወድም ።

**ጣዖት ያመለኩትን ሕዝብእግዚአብሔር አጠፋቸው ፤ በቤትህ ውስጥ ጣዖት አይገኝ !**

ዘዳግም ፡ 7÷ 24 - 26

ነገሥታቶቻቸውንም ፡ በእጅህ ፡ አሳልፎ ፡ ይሰጣቸዋል ÷ ስማቸውንም ፡ ከሰማይ ፡ በታች ፡ ታጠፋለህ፤ እስክታጠፋቸው ፡ ድረስ ፡ ማንም ፡ በፊተህ ፡ ይቆም ፡ ዘንድ ፡ አይችልም ። የተቀረጸውንም ፡ የአምላኮቻቸውን ፡ ምስል ፡ በእሳት ፡ ታቃጥላለህ ፤ የተሠራባቸውን ፡ ብርና ፡ ወርቅ ፡ አትመኝ፤ በአምላክህም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ርኩስ ፡ ነውና ፡ እንዳትጠመድበት ፡ ከእርሱ ፡ ምንም ፡ አትውሰድ ። እንደ ፡ እርሱም ፡ ርጉም ፡ እንዳትሆን ፡ ርኩስን ፡ ነገር ፡ ወደ ፡ ቤትህ ፡ አታግባ ፤

**በክርስቶስ ምድራዊ አገልግሎት ዘመን እግዚአብሔር በመረጣቸው ሕዝቦች መካከል ለምን በዲያቢሎስ የተያዙ ሰዎች ይበዙ ነበር ? ቅድመ አያቶቻቸው ጣዖትን ያመልኩ ነበርና ነው ።**

መዝሙረ ፡ ዳዊት ፡ 106 ÷ 36 - 37 ፡ 40

ለጣዖቶቻቸውም ፡ ተገዙ ÷ ወጥመድም ፡ ሆኑባቸው ።

ወንዶች ፡ ልጆቻቸውንና ፡ ሴቶች ፡ ልጆቻቸውን ፡ ለአጋንንት ፡ ሠዉ ፡

የእግዚአብሔርም ፡ ቍጣ ፡ በሕዝቡ ፡ ላይ ፡ ነደደ ÷

ርስቱንም ፡ ተጸየፈ ።

## በጣዖት ማምለክ ያስቀጣል

ዮሐንስ ፡ ራእይ ፡ 21÷ 8

ጣዖትንም ፡ የሚያመልኩ ፡ የሐሰተኞዎችም ፡ ሁሉ ፡ ዕድላቸው ፡ በዲንና ፡ በእሳት ፡ በሚቃ ጠል ፡ ባሕር ፡ ነው ፡ ይኸውም ፡ ሁለተኛ ፡ ሞት ፡ ነው ።

## ጥንቆላ ሁሉ ኃጢአት ነው

ዘጸአት ፡ 22÷18

መተተኛይቱን ፡ በሕይወት ፡ እንድትኖር አትፍቀድላት ።

ሚ ክ ያ ስ ፡ 5÷12

አፈ ርሳለሁ ፡ መተትንም ፡ ከእጅህ ፡ አጠፋለሁ ÷ ምዋርተኞችም ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አይሆኑ ልህም ፤

1 ሳሙኤል ፡ 15÷23

ዓመፀኛ ነት ፡ እንደ ፡ ምዋርተኛ ፡ ኃጢአት ÷ እልከኝነ ትም ፡ ጣዖትንና ፡ ተራፊምን ፡ እንደ ፡ ማም ለክ ፡ ነው ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ንቀሃልና ፡ እግዚአብሔር ፡ ንጉሥ ፡ እንዳትሆን ፡ ናቀህ ፡ አለ ።

ዘዳግም ፡ 18÷9 - 12

አምላክህ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወደሚሰጥህ ፡ ምድር ፡ በገባህ ፡ ጊዜ ፡ እነዚያ ፡ አሕዛብ ፡ የሚ ያደርጉትን ፡ ርኵሰት ፡ ታደርግ ፡ ዘንድ ፡ አት ማር ። ወንድ ፡ ልጁን ፡ ሴት ፡ ልጁን ፡ በእሳት ፡ የሚያሳልፍ ÷ ምዋርተኛም ÷ ሞራ ፡ ገላጭም ÷ አስማተኛም ÷ መተተኛም ÷ በድግምት ፡ የሚ ጠነቀ-ልም ÷ መናፍስትንም ፡ የሚጠራ ÷ ጠን ቋይም ÷ ሙታን ፡ ሳቢም ፡ በአንተ ፡ ዘንድ ፡ አይ ገኝ ። ይህንም ፡ የሚያደርግ ፡ ሁሉ ፡ በእግዚአ ብሔር ፡ ፊት ፡ የተጠላ ፡ ነው ፤ ስለዚህም ፡ ርኵ ሰት ፡ አምላክህ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከፊትህ ፡ ያሳ ድዳቸዋል ።

## እግዚአብሔር ከከብ ቆጠ ራን ፤ ሟርትን ፤ ሰውነትን በስ ለት ማቁሰልንና መቁረጥን ይከለክላል

ዘሌዋውያን፡19÷26 ፣ 28

ከደሙ ፡ ጋር ፡ ምንም ፡ አትብሉ ፡ አስማ ትም ፡ አታድርጉ ፡ ሞራ ፡ ገላጭም ፡ አትሁኑ ።

ስለ፡ሞተውም፡ሥጋችሁን፡አትንጩ ÷ ገላችሁንም፡አትንቀሱት፡እኔ፡እግዚአብሔር፡ ነኝ ።

ኤ ር ም ያ ስ 27÷9

ነቢያቶቻችሁንና ፡ ምዋርተኞቻችሁን÷ ሕልም፡ አላሚዎቻችሁንና ፡ ቃላተኞቻችሁን ፡ መተተ ኞቻችሁንም ፡ አትስሙ ።

ሚ ል ክ ያ ስ ፡ 3÷5

በመተተኞችና ፡ በአመንዝ ሮች ÷ በሐሰትም ፡ በሚምሉ ÷ የምንደኛውን ፡ ደመወዝ፡ በሚከለክሉ ÷ መበለቲቱንና ፡ ድሀ፡ አደጉን ፡ በሚያስጨንቁ ÷ የመጻተኛውንም ፡ ፍርድ፡ በሚያጣምሙ ÷ እኔንም ፡ በማይፈሩ ፡ ላይ፡ ፈጣን፡ ምስክር፡ እሆንባቸዋለሁ ÷

ተራፊም ፡ ከንቱነትን ፡ ተናግረዋልና ÷ ምዋርተኞችም ፡ ውሸትን ፡ አይተዋልና ፡ ሕል ምንም ፡ የሚያዩ ፡ በሐሰት ፡ ተናግረዋል ÷ በከ ንቱም ፡ ያጽናናሉ ፡ እረኛም ፡ የላቸውምና ፡ እንደ ፡ በጎች ፡ ተቅበዘበዘዋል ፡ ተጨንቀው ማል ። —ዘ ካ ር ያ ስ ፡ 10 ÷ 2

## በእውነተኛው እረኛ ታመኑ

ዮሐንስ፡ 14÷1

ልባችሁ አይታወክ ፡ በእግዚአብሔር እመኑ በእኔም ፡ ደግሞ ፡ እመኑ ።

## ሙታን ሳቢን መጠየቅን

እነርሱም ፡— የሚጮኹትንና ፡ ድምፃቸ ውን ፡ ዝቅ ፡ አድርገው ፡ የሚናገሩትን ፡ መናፍ ስት ፡ ጠሪዎችንና ፡ ጠንቋዮችን ፡ ጠይቁ ፡ ባሉ አችሁ ፡ ጊዜ ÷ ሕዝቡ ፡ ከአምላኩ ፡ መጠየቅ ፡ አይገባውምን ? —ኢ ሳ ይ ያ ስ ፡ 8 ÷ 19

## ሞራ ገላጭን ማማከርን

የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ምዋርቱን ፡ ያም ዋርት ፡ ዘንድ ፡ በመንታ ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ በሁ ለቱ ፡ መንገዶች ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ቆሞ ፡ ነበር ፡ ፍላጻ ችን ፡ ወዘወዘ ÷ ከተራፊምም ፡ ጠየቀ ÷ ጉበትም ፡ ተመለከተ ። —ሕዝቅኤል ፡ 21 ÷ 21

## በበትር መጠንቆልን

የግልሙትና ፡ መንፈስ ፡ ሕዝቤን ፡ አስቶአቸዋልና ÷ እነርሱም ፡ ከአም ላካቸው ፡ ርቀው ፡ አመንዝረዋልና ፡ በትራቸ ውን ፡ ይጠይቃሉ ÷ ዘንጋቸውም ፡ ይመልስላቸ ዋል ። —ሆ ሴ ዕ ፡ 4 ÷ 12

## በርግማን መበቀልን

1 ዜና ፡ 10 ÷ 13 ፣ 14

እንዲሁ ፡ ሳኦል ፡ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ ስላ ደረገው ፡ ኃጢአት ÷ የእግዚአብሔርንም ፡ ቃል ፡ ስላልጠበቀ ፡ ሞተ ። ደግሞም ፡ መናፍስት ፡ ጠሪ ፡ ስለ ፡ ጠየቀ ፡ እግዚአብሔርንም ፡ ስላል ጠየቀ ÷ ስለዚህ ፡ ገደለው ÷

ሚ ክ ያ ስ ፡ 3 ÷ 7

ከእግዚአብሔርም ፡ ዘንድ ፡ መልስ ፡ የለምና ፡ ባለ ፡ ራእዮቹ ፡ ያፍራሉ ÷ ምዋርተኞችም ፡ ይዋ ረዳሉ ፡ ሁሉም ፡ ከንፈራቸውን ፡ ይሸፍናሉ ።

## አሕዛብ የሰማይ ምልክቶችን ይከተላሉ

ኤ ር ም ያ ስ፡ 10 ÷ 2

እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡— የአሕዛብን፡ መንገድ፡ አትማሩ ፡ ከሰማይ፡ ምልክትም፡ አትፍሩ ፡ አሕዛብ ፡ ይፈሩታልና ።

**ጎሩ ዕድል ይሰጡኛል ብለህ በተለያዩት ፈደላት ወይምሌላ ነገሮች አትመን፥ ምኞትን የሚቀሰቅሱትን ሥዕሎች ወይም ዘፈኖች አይኑሩህ። በፊቴ ምንም ክፉ ነገር አላኖርም በል፥ መዝ. 101፥3።**

ማቴዎስ፡ 23 ÷ 27 - 28

እናንተ ፡ ግብዞች ፡ ጻፎችና ፡ ፈሪሳውያን ÷ በውጭ ፡ አምረው ፡ የሚታዩ ፡ በውስጥ ፡ ግን ፡ የሙታን፡ አጥንት፡ ርኵሰትም፡ ሁሉ ፡ የተሞሉ፡ በኖራ ፡ የተለሰኑ ፡ መቃብሮችን ፡ ስለምትመስሉ ፡ ወዮላችሁ ። እንዲሁ ፡ እናንተ ፡ ደግሞ ፡ በውጭ፡ ለሰው ፡ እንደ፡ ጻድቃን፡ ትታያላችሁ፡ በውስጣችሁ ፡ ግን ፡ ግብዝነትና ፡ ዓመፃኝነት ፡ ሞልቶባችኋል ።

## ራስን መግደል የዲያብሎስ አሳብ ነው

በራስህ እጅ ብትሞት ከችግርና ከጥፋተኛነት ትላቀቃለህ የሚለውን የሰይጣንና የአጋንንትን ምክር አትቀበል፥ አትግደል ይላል — ዘፀ. 20፥13 ።

## ከኃጢአተኞች ነቢያት የመ ጡትን

ኤ ር ም ያ ስ፡14÷14

እግዚአብሔርም፡እንዲህ አለኝ፡— ነቢያቱ፡ውሸት፡በስሚ፡ትንቢት፡ይናገራሉ፡ አላክኋቸውም÷አላዘዝኋቸውም÷አልተናገ ርኋቸውም፡የውሸቱን፡ራእይ፡ምዋርትንም፡ ከንቱንም፡ነገር፡የልባቸውንም፡ሽንገላ፡ይሰ ብኩላችኋል።

ማርቆስ፡13÷22

አተመኑ፡ሐሰተኞች፡ክርስቶሶችና፡ሐሰተ ኞች፡ነቢያት፡ይነሣሉና፡ቢቻላቸውስ፡የተ መረጡትን፡እንኳ፡ያስቱ፡ዘንድ፡ምልክትና፡ ድንቅ፡ያደርጋሉ።

## ሙታንን በማነጋገር በኩል የተገኙትን

2 ሳሙኤል፡12÷23

አሁን፡ግን፡ሞቶአል፡የምጾመው፡ስለ፡ ምንድር፡ነው? በውኑ፡እንግዲህ፡እመልሰው፡ ዘንድ፡ ይቻለኛልን? እኔ፡ወደ፡እርሱ፡ እሄዳለሁ፡ እንጂ፡ እርሱ፡ወደ፡እኔ፡ አይመለስም፡አለ።

## ከአጋንንት ጋር አትነጋገር፣ እንዲተውሀ በክርስቶስ ስም እ ዘዛቸው። በተለያዩት የጥንቆላ ዘዴዎች አትመን፣ ደኅንነት ከ ጌታ ነው፣ ምሳሌ 21፣31።

## ጣዖታትንና የሰይጣን መጻሕ ፍትን አጥፋ

## ሩካቤ ሥጋ የተወሰነው ለጋብቻ ብቻ ነው

ዘፍጥረት ፡ 2 ÷ 22 - 24 እግዚአ ብሔር ፡ አምላክም፡ ከአዳም ፡ የወሰዳትን ፡ አጥ ንት ፡ ሴት ፡ አድርጎ ፡ ሠራት ፡ ወደ ፡ አዳምም ፡ አመጣት ። አዳምም ፡ አለ ፡- ይህች ፡ አጥንት ፡ ከአጥንቴ ፡ ናት ፡ ሥጋም ፡ ከሥጋዬ ፡ ናት ፡ እር ስዋ ፡ ከወንድ ፡ ተገኝታለችና ፡ ሴት ፡ ትባል ። ስለዚህ ፡ ሰው ፡ አባቱንና ፡ እናቱን ፡ ይተዋል ÷ በሚስቱም ፡ ይጣበቃል ፤ ሁለቱም ፡ አንድ ፡ ሥጋ ፡ ይሆናሉ ።

ዕብራውያን ፡ 13 ÷ 4

መጋባት ፡ በሁሉ ፡ ዘንድ ፡ ክቡር ፡ መኝታውም ፡ ንጹሕ ፡ ይሁን። ሴሰኞችንና ፡ አመንዝሮችን ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ ይፈርድባቸዋል ።

ኤፌሶን ፡ 5 ÷ 5

ይሁን ፡ እወቁ ፡ አመንዝራም ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ ርኵስ ፡ ወይም ፡ የሚመኝ ፡ እርሱም ፡ ጣዖትን ፡ የሚያመልክ ፡ በክርስቶስና ፡ በእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ ርስት ፡ የለውም ።

**ሩካቤ ሥጋ ራስህን ለሌላ ሰው በመስጠት ረገድ ከፍ ያለ ድርጊት ነው ። በዚህ ምክንያት በጋብቻ ሥርዓት ውስጥ ብቻ ተፈቅዷል ። በምንዝርና ምክንያት ብቻ እግዚአብሔር መፋታትን ፈቅዷል ፤ አመንዝሪው ከጋብቻ ሕግ ውጭ ለሌላ ሰው ራሱን በመስጠት የጋብቻ ቃል ኪዳን አፍርሷል ።**

# አመንዝራነትና ዘማዊነት በእግዚአብሔር ላይ ማመጽ ነው

አታመንዝር ። — ዘጸአት፡20÷14

ይህ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ እርሱም ፡ መቀ ደሳችሁ፡ነውና ፡ ከዝሙት ፡እንድትርቁ ። — 1 ተሰሎንቄ ፡ 4÷3

ማናቸውም፡ ሰው ፡ ከሌላ ፡ ሰው ፡ ሚስት ፡ ወይም ፡ ከባልንጀራው ፡ ሚስት ፡ ጋር ፡ ቢያመ ነዝር ፡ አመንዝራውና ፡ አመንዝራይቱ ፡ ፈጽ መው ፡ ይገደሉ ። — ዘሌዋውያን፡20÷10

## በሥጋህ ላይ የምትሠራው ኃጢአት

ሥጋ ፡ ግን ፡ ለጌታ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ለዝሙት ፡ አይደለም ። ሥጋችሁ ፡ የክርስቶስ ፡ ብልቶች ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አታውቁምን? ከዝሙት ፡ ሽሹ ። ሰው ፡ የሚያደርገው ፡ ኃጢአት ፡ ሁሉ ፡ ከሥጋ ፡ ውጭ ፡ ነው ፡ ዝሙትን ፡ የሚሠራ ፡ ግን ፡ በገዛ ፡ ሥጋው ፡ ላይ ፡ ኃጢአትን ፡ ይሠራል ። — 1 ቆሮንቶስ ፡ 6÷13፣15፣18

## ወላጆች ልጆቻቸውን መጠበቅ አለባቸው

ምድሪቱ ፡ ከግልሙትና ፡ ከርኩሰትም ፡ እንዳ ትሞላ ፡ ሴት ፡ ልጅህን ፡ ታመነዝር ፡ ዘንድ ፡ አታ ክሳት ። — ዘሌዋውያን፡19÷29

1 ቆሮንቶስ :15÷22

ሁሉ ፡ በአዳም ፡ እንደሚሞቱ ፡ እንዲሁ ፡ ሁሉ ፡ በክርስቶስ ፡ ደግሞ ፡ ሕያዋን ፡ ይሆናሉና ።

ዕብራውያን :2÷14 - 15

እንግዲህ ፡ ልጆቹ ፡ በሥጋና ፡ በደም ፡ ስለሚ ካፈሉ ÷ እርሱ ፡ ደግሞ ፡ በሞት ፡ ላይ ፡ ሥልጣን ፡ ያለውን ፡ በሞት ፡ እንዲሽር ÷ ይኸውም ፡ ዲያ ብሎስ ፡ ነው ÷ በሕይወታቸውም ፡ ሁሉ ፡ ስለ ፡ ሞት ፡ ፍርሃት ፡ በባርነት ፡ ይታሰሩ ፡ የነበሩትን ፡ ሁሉ ፡ ነጻ ፡ እንዲያወጣ ÷ በሥጋና ፡ በደም ፡ እን ዲሁ ፡ ተካፈለ ።

1ዮሐንስ ፡ 3÷8

ስለዚህ ፡ የዲያብሎስን ፡ ሥራ ፡ እንዲያ ፈርስ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ተገለጠ ።

ቈላስይስ ፡ 2÷15

አለቅነትንና ፡ ሥልጣናትን ፡ ገፎ ፡ ድል ፡ በመንሣት ፡ በእርሱ ፡ እያዘ ራቸው ፡ በግልጥ ፡ አሳያቸው ።

## በክርስቶስ በኩል የዘላለም ሕይወት አግኝተናል

2 ጢሞቴዎስ ፡ 1÷ 9 - 10

ያዳነን ፡ በቅ ዱስም ፡ አጠራር ፡ የጠራን ፡ እግዚአብሔር ፡ ነውና ፡ ይህም ፡ እንደ ፡ ራሱ ፡ አሳብና ፡ ጸጋ ፡ መጠን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ ሥራችን ፡ መጠን ፡ አይደለም ፡ ይህም ፡ ጸጋ ፡ ከዘላለም ፡ ዘመናት ፡ በፊት ፡ በክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ ተሰጠን ።

# ክርስቲያኖች በሰይጣን ላይ ያላቸው ድል

1ጴጥሮስ፡ 5÷8-9

ባላጋራችሁ፣ዲያብሎስ፣የሚውጠውን፣ፈልጎ፡ እንደሚያገሣ፣ አንበሳ፣ ይዞራልና ፡ በዓለም ፡ ያሉት፣ወንድሞቻችሁ፣ያን፣መከራ፡በሙሉ፡ እንዲቀበሉ ፣ እያወቃችሁ ፡ በእምነት ፣ ጸንታ ችሁ፣ተቃወሙት ።

ኤፌሶን፡6÷11-18

የዲያብሎስን ፡ ሽንገላ ፡ ትቃ ወሙ ፡ ዘንድ ፡ ዘንዲቻላችሁ ፡ የእግዚአብሔ ርን፣ ዕቃ፡ ጦር፡ ሁሉ፡ ልበሱ ። መጋደላችን፡ ከደምና ፡ ከሥጋ ፡ ጋር ፡ አይደለምና ÷ ከአለቆ ችና ፡ከሥልጣናት፣ ጋር ፡ከዚህም ፡ከጨለማ፡ ዓለም ፡ ገዦች ፡ ጋር ፡ በሰማያዊም ፡ ስፍራ ፡ ካለ፣ ከክፋት፣ መንፈሳውያን፡ ሠራዊት፡ ጋር፡ ነው፣ እንጂ ። ስለዚህ ፡በክፉው፣ቀን፣ለመቃ ወም÷ሁሉንም ፡ ፈጽማችሁ ፡ ለመቆም ፡ እን ድትችሉ፣ የእግዚአብሔርን፡ዕቃ፡ጦር፡ሁሉ፡ አንሡ ። እንግዲህ ፣ ወገባችሁን ፡ በእውነት ፣ ታጥቃችሁ÷የጽድቅንም ፣ ጥሩር፣ለብሳችሁ÷ በሰላም፡ወንጌልም፡በመዘጋጀት፣እግሮቻችሁ፡ ተጫምተው፡ ቁሙ ፤ በሁሉም ፡ ላይ ፡ጨም ራችሁ ፡የሚንበለበሉትን ፡ የክፉውን ፡ ፍላጸ ዎች ፡ ሁሉ ፡ ልታጠፉ ፡የምትችሉበትን ፡ የእ ምነትን፡ ጋሻ ፣ አንሡ ፤ የመዳንንም ፡ ራስ ፡ ቍር ፡ የመንፈስንም፡ ሰይፍ ፣ ያዙ ፣ እርሱም፡ የእግዚአብሔር፡ ቃል፡ነው ። በጸሎትና፡ በል መናም ፡ ሁሉ ፡ ዘወትር ፡ በመንፈስ ፣ ጸልዩ ፤

ያዕቆብ፡ 4÷7

እንግዲህ ፡ ለእግዚአብሔር፡ ተገዙ ፡ ዲያብሎስን፡ ግን፡ተቃወሙ፡ ከእናንተም፡ ይሸሻል ።

1ዮሐንስ፡ 4 ÷ 4

በዓለም ፡ ካለው ፡ ይልቅ፡በእናንተ ፡ ያለው ታላቅ ፡ ነውና ።

**ሰይጣን ለምን ይሸሻል፣ ክርስቶስ በውስጥህ ነውና!**

# እርሱ የእግዚአብሔር ቃልነው

ዕብራውያን ፡ 1÷1 - 2

ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ እግዚአብሔር ፡ በብዙ ፡ ዓይነት ተናግሮ ፡ ሁሉን ፡ ወራሽ ፡ ባደረገው ፡ ደግሞም ፡ ዓለማትን ፡ በፈጠረበት ፡ በልጁ ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ መጨረሻ ፡ ለእኛ ፡ ተናገረን ።

ማርቆስ ፡ 1÷22

እንደ ፡ ባለ ፡ ሥልጣን ፡ ያስተምራቸው ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ ጻፎች ፡ አይደለምና ፡ በትምህርቱ ፡ ተገረሙ ።

1 ቆሮንቶስ ፡ 8÷6

ለእኛስ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ከእርሱ ፡ የሆነ ፡ እኛም ፡ ለእርሱ ፡ የሆንን ፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ አብ ፡ አለን ፡ ነገር ፡ ሁሉም ፡ በእርሱ ፡ በኩል ፡ የሆነ ፡ እኛም ፡ በእርሱ ፡ በኩል ፡ የሆ ንን ፡ አንድ ፡ ጌታ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አለን ።

ዮሐንስ ፡ 5÷27

የሰው ፡ ልጅም ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ይፈርድ ፡ ዘንድ ፡ ሥልጣን ፡ ሰጠው ።

1 ጴጥሮስ ፡ 3÷22

እርሱም ፡ መላእክትና ፡ ሥልጣናት ፡ ኃይላትም ፡ ከተገዙለት ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ሄዶ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቀኝ ፡ አለ ።

ሮሜ ፡ 14÷9

ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ሙታንንም ፡ ሕያዋንንም ፡ ይገዛ ፡ ዘንድ ፡ ክርስቶስ ፡ ሞቶአልና ፡ ሕያውም ፡ ሆኖአልና ።

ማቴዎስ ፡ 28÷18

ኢየሱስም ፡ ቀረበና ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገራቸው ፡– ሥልጣን ፡ ሁሉ ፡ በሰማይና ፡ በምድር ፡ ተሰጠኝ ።

ማርቆስ ፡ 4÷39

ነቅቶም ፡ ነፋ ሱን ፡ ገሠጸው ፡ ባሕሩንም ፡ – ዝም ፡ በል ፡ ፀጥ ፡ በል ፡ አለው ። ነፋሱም ፡ ተወ ፡ ታላቅ ፡ ዐጥ ታም ፡ ሆነ ።

## በሥልጣን ፈወሰ

ማርቆስ ፡ 2÷10-12

ነገር ፡ ግን ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ኃጢአትን ፡ ሊያስተሰርይ ፡ ሥልጣን ፡ እን ዳለው ፡ እንድታውቁ ፡ ሽባውን ፡ — አንተን ፡ እል ሃለሁ ፡ ተነሣ ፡ አልጋህን ፡ ተሸከምና ፡ ወደ ፡ ቤትህ ፡ ሂድ ፡ አለው ። ተነሥቶም ፡ ወዲያው ፡ አልጋውን ፡ ተሸክሞ ፡ በሁሉ ፡ ፊት ፡ ወጣ ፡ ስለዚህም ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ተገረሙና ፡ – እንዲህ ፡ ያለ ፡ ከቶ ፡ አላየንም ፡ ብለው ፡ እግዚአብሔርን ፡ አከበሩ ።

## ክርስቶስ አጋንንትን አስወጣ

ማርቆስ ፡ 1÷26-27

ርኵሱም ፡ መንፈስ ፡ አንፈራገጠውና ፡ በታላቅ ፡ ድምፅ ፡ ጮኾ ፡ ከእርሱ ፡ ወጣ ። ሁሉም ፡ — ይህ ፡ ምን ድር ፡ ነው ? በሥልጣን ፡ ርኵሳን መናፍስትን ፡ ያዝዛል ፡ እነርሱም ፡ ይታዘዙለታልና ፡ ይህ ፡ አዲስ ፡ ትምህርት ፡ ምንድር ፡ ነው ? ብለው ፡ እስኪጠያየቁ ፡ ድረስ ፡ አደነቁ ።

## በሥልጣኑ የሞቱትን አስነሣ

ሉቃስ ፡ 7÷14-15

አለውም ፡ — አንተ ፡ ጐበዝ ፡ እልሃለሁ ፡ ተነሣ ። የሞተውም ፡ ቀና ፡ ብሎ ፡ ተቀመጠ ፡ ሊናገርም ፡ ጀመረ ፡ ለእናቱም ፡ ሰጣት ።

# የክርስቶስ ተከታዮች በጠ ላት ሁሉ ላይ ሥልጣንና ኃይል አላቸው

ሉቃስ ፡ 10÷19

እነሆ ፥ እባቡንና ፣ ጊንጡን ፣ ትረግጡ ፣ ዘንድ ፥ በጠላትም ፣ ኃይል ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፣ ሥል ጣን ፣ ሰጥቻችኋለሁ የሚጐዳችሁም ፣ ምንም ፡ የለም ።

ሉቃስ ፡ 9÷1

አሥራ ፣ ሁለቱንም ፣ ሐዋርያት ፡ በአንድነት ፣ ወደ ፣ እርሱ ፣ ጠርቶ ፣ በአጋንንት ፣ ሁሉ ፣ ላይ ፣ ደዌንም ፣ ይፈውሱ ፣ ዘንድ ፡ ኃይልና ፣ ሥልጣን ፡ ሰጣቸው ።

ማርቆስ ፡ 11÷23

እውነት ፡ እላትኋለሁ ፥ ማንም ፡ ያለው ፡ ነገር ፡ እንዲደረግ ለት ፡ ቢያምን ፡ በልቡ ፡ ሳይጠራጠር ፥ ይሆን ፡ ተራራ ፡ -- ተነቅለህ ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ተወርወር ፡ ቢል ፡ ይሆንለታል ።

ዮሐንስ ፡ 14 ÷ 12

እውነት ፡ እውነት ፡ እላችኋለሁ ፡ በእኔ ፡ የሚ ያምን ፡ እኔ ፡ የማደርገውን ፡ ሥራ ፡ እርሱ ፡ ደግሞ ፡ ያደርጋል ።

ማርቆስ ፡ 9 ÷ 23

ኢየሱስም ፣— ቢቻልህ ፣ ትላለህ ፣ ለሚያምን ፣ ሁሉ ፣ ይቻላል ፣ አለው ።

ኤፌሶን ፡ 1÷ 19

ለምናምንም ፣ ከሁሉ ፣ የሚበልጥ ፡ የኃይሉ ፡ ታላቅነት ፣ ምን ፡ እንዲሆን ፣ ታውቁ ፡ ዘንድ ፡ ነው ።

## ገሥጹአቸው ፣ እንዲወጡ በኢየሱስ ስም እዘዙአቸው

ማርቆስ ፡ 5÷8-9 ፣ 13

አንተ ፡ ርኵስ ፡ መንፈስ ፥ ከዚህ ፡ ሰው ፡ ውጣ ፡ ብሎት ፡ ነበርና ። ስምህ ፡ ማን ፡ ነው ? ብሎ ፡ ጠየቀው ። ብዙዎች ፡ ነንና ፡ ስሜ ፡ ሌጌዎን ፡ (1) ነው ፡ አለው ፡ ርኵሳን ፡ መናፍስቱም ፡ ወጥተ ው ፡ ወደ እሪያዎቹ ፡ ገቡ ።

ማርቆስ ፡ 9 ÷ 25-27 ፣ 29

ኢየሱስም ፡ . . . . . ርኵሱን ፡ መንፈስ ፡ ገሠ ጸና ፡— አንተ ፡ ዲዳ ፡ ደንቆሮም ፡ መንፈስ ፥ እኔ ፡ አዝሃለሁ ፥ ከእርሱ ፡ ውጣ ፡ እንግዲህም ፡ አትግ ባበት ፡ አለው ። ጮኾም ፡ እጅግም ፡ አንፈራግ ጦት ፡ ወጣ ፡ ብዙዎችም ፡ — ሞተ ፡ እስኪሉ ፡ ድረስ ፡ እንደ ፡ ሙት ፡ ሆነ ። ኢየሱስ ፡ ግን ፡ እጁን ፡ ይዞ ፡ አስነሣው ፡ ቆመም ። . . . . ይህ ፡ ወገን ፡ በጸሎትና ፡ በጦም ፡ ካልሆነ ፡ በምንም ፡ ሊወጣ ፡ አይችልም ፡ አላቸው ።

የሐዋርያት ፡ ሥራ 16÷18

ጳወሎስ ፡ ግን ፡ ተቸገረና ፡ ዘወር ፡ ብሎ ፡ መ ንፈሱን ፡ – ከእርስዋ ፡ እንድትወጣ ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡ አዝሃለሁ ፡ አለው ፡ በዚያም ፡ ሰዓት ፡ ወጣ ።

ሉቃስ ፡ 4÷35

ኢየሱስም ፡— ዝም ፡ በል ፡ ከእርሱም ፡ ውጣ ፡ ውም ፡ ገሠጸው ። ጋኔኑም ፡ በመካከላቸው ፡ ጥሎት ፡ ሳይጐዳው ፡ ከእርሱ ፡ ወጣ ።

## ክርስቶስ ብርሃንና ሰላምን ይሰጣል

ሉቃስ ፡ 1÷79

ብርሃኑም ፡ በጨለማና ፡ በሞት ፡ ጥላ ፡ ተቀምጠው ፡ ላሉት ፡ ያበ ራል፡ እግሮቻችንንም ፡ በሰላም ፡ መንገድ፡ ያቀናል ።

2 ተሰሎንቄ፡ 3÷16

የሰላምም ፡ ጌታ ፡ ራሱ ፡ በሁሉ ፡ መንገድ ፡ ዘወትር ፡ ሰላምን ፡ ይስጣችሁ ።

## አጋንንትና ሰይጣን ሰውን ያጠፋሉ

ዮሐንስ ፡ 10÷10

ሌባው ፡ ሊሰርቅና ፡ ሊያርድ ፡ ሊያጠፋም፡ እንጂ ፡ ስለ ፡ ሌላ፡ አይመ ጣም ።

የዮሐንስ፡ ራእይ፡ 12÷12

ለምድርና ፡ ለባሕር፡ ወዮላቸው ዲያብሎስ ፡ ጥቂት ፡ ዘመን ፡ እንዳለው ፡ አውቆ ፡ በታላቅ፡ ቍጣ ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ ወርዶአልና ።

## ሰይጣን ጨለማንና ስቃይን ይሰጣል

ምሳሌ ፡ 4÷19

የኀጥአን ፡ መንገድ ፡ እንደ ፡ ጨለማ፡ ነው እንዴት፡ እንደሚሰናከሉም ፡ አያውቁም ።

ሉቃስ ፡ 16÷22-23

ባለ ፡ ጠጋው ፡ ደግሞ ፡ሞተና ፡ ተቀበረ ። በሲኦልም ፡ በሥቃይ ፡ ሳለ ፡ አሻቅቦ ፡ አብርሃ ምን ፡ በሩቅ ፡ አየ ።

# የክርስቶስና የሰይጣን ሥራዎች

## ክርስቶስ እውነት ነው

ዮሐንስ፣1፥14 ፤ 8፥31-32

ቃልም ፣ ሥጋ፣ ሆነ ፣ ጸጋንና ፣ እውነትንም ፣ ተመልቶ ፣ በእኛ ፣ አደረ ፥ አንድ ፣ ልጅም ፣ ከአባቱ ፣ ዘንድ ፣ እንዳለው፣ክብር ፣ የሆነውን ፣ ክብሩን ፣ አየን ። . . . . . . -እናንተ፣ በቃሌ ፣ ብትኖሩ ፣ በእውነት ፣ ደቀ ፣ መዛሙርቴ፣ ናችሁ ፣ እውነትንም ፣ ታውቃላችሁ ፣ እውነትም ፣ አርነት ፣ ያወጣችኋል ፣ አላቸው ።

## ክርስቶስ በፍቅር የተሞላ ነው

1 ዮሐንስ፣ 3፥16

እርሱ ፣ ስለ ፣ እኛ ፣ ነፍሱን ፣ አሳልፎ ፣ ሰጥቶእልና ፣ በዚህ ፣ ፍቅርን ፣ አውቀናል ፣ እኛም ፣ ስለ ፣ ወንድሞቻችን ፣ ነፍሳችንን ፣ አሳልፈን ፣ እንድንሰጥ ፣ ይገባናል ።

## ሰይጣን የውሸት አባት ነው

ዮሐንስ ፣8፥44

እናንተ ፣ ከአባታችሁ ፣ ከዲያብሎስ ፣ ናችሁ የአባታችሁንም ፣ምኞት ልታደርጉ፣ትወዳላችሁ ። እርሱ፣ከመጀመሪያ፣ነፍስ ፣ገዳይ ፣ ነበረ ፣ እውነትም ፣በእርሱ ፣ ስለ ፣ ሌለ ፣ በእውነት ፣ አልቆመም ። ሐሰትን ፣ ሲናገር ፣ ከራሱ ፣ ይናገራል ሐሰተኛ ፣ የሐሰትም ፣ አባት ፣ ነውና ።

## ሰይጣን ጥላቻን ያስተምራል

ገላትያ፣ 5፥19-20

የሥጋ፣ሥራም፣ የተገለጠ ፣ ነው ፣ እርሱም ፣ ዝሙት ርኵሰት መዳራት ፣ ጣዖትን ፣ ማምለክ ፣ ምዋርት ፣ ጥል ፣ ክርክር ቅንዓት ቍጣ፣ . . . .

## ክርስቶስ ልብን ያነፃል

1ዮሐንስ፡1፥7

ነገር፡ግን፡እርሱ፡በብርሃን፡እንዳለ፡በብርሃን፡ብንመላለስ፡ለእያንዳንዳችን፡ኅብረት፡አለን፡የልጁም፡የኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ደም፡ከኃጢአት፡ሁሉ፡ያነጻናል ።

## ክርስቶስ ከኃጢአት ያድናል

ሮሜ፡5፥9

ይልቁንስ፡እንግዲህ፡አሁን፡በደሙ፡ከጸደቅን፡በእርሱ፡ከቍጣው፡እንድናለን ።

## ክርስቶስ የዘለዓለም ሕይወትን ይሰጣል

ዮሐንስ፡17፥3

እውነተኛ፡አምላክ፡ብቻ፡የሆንህ፡አንተን፡የላክኸውንም፡ኢየሱስ፡ክርስቶስን፡ያውቁዘንድ፡ይህች፡የዘላለም፡ሕይወት፡ናት ።

## ሰይጣን ልብን ያረክሳል

ገላትያ፡6፥7-8

አትሳቱ፡እግዚአብሔር፡አይዘበትበትም ። ሰው፡የሚዘራውን፡ሁሉ፡ያንኑ፡ደግሞ፡ያጭዳልና፡በገዛ፡ሥጋው፡የሚዘራ፡ከሥጋ፡መበስበስን፡ያጭዳልና ።

## ሰይጣን ኃጢአትን ወደ መሥራት ይመራል

1ዮሐንስ 3፥8

ኃጢአትን፡የሚያደርግ፡ከዲያብሎስ፡ነው፡ዲያብሎስ፡ከመጀመሪያ፡ኃጢአትን፡ያደርጋልና ።

## ሰይጣን ወደ ዘለዓለም ሞት ይመራል

ዮሐንስ፡14÷30
ከእንግዲህ፡ወዲህ፡ከእናንተ ፡ ጋር ፡ ብዙ ፡ አ ልናገርም ፡ የዚህ ፡ ዓለም ፡ ገዥ ፡ ይመጣልና ፡ በእኔ ፡ ላይም ፡ አንዳች ፡ የለውም ።

## ብጥብጥንና ትርምስምስን የ ሚፈጥረው እርሱ ነው

ያዕቆብ፡3÷15-16
ይህ፡ ጥበብ፡ከላይ፡የሚወርድ፡አይደለም ፡ ነገር፡ ግን፡የምድር፡ነው ፡ የሥጋም ፡ ነው ፡ የ አጋንንትም፡ነው ፡ ቅንዓትና፡አድመኛነት፡ በ ሉበት፡ ስፍራ ፡ በዚያ ፡ ሁከትና ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ አሉና ።

## እድል ሲገጥመው ሰይጣን የአምልኮ ነፃነት ይከለክላል። የልብ እምነት ሊከለክል አ ይችልም ።

## እምነትህን አትልቀቅ !

## እስከ ሞት ድረስ ለክርስቶስ እውነተኛ ሁንለት

የሐዋርያት ፡ ሥራ፡7÷59-60
እስጢፋኖስም ፡— ጌታ፡ ኢየሱስ ፡ ሆይ ፡ ነፍሴን ፡ ተቀበል ፡ ብሎ ፡ ሲጠራ ፡ ይወግ ሩት ፡ ነበር ። ተንበርክኮም ፡ ጌታ ፡ ሆይ ፡ ይህን ፡ኃጢአት፡አትቍጠርባቸው ፡ ብሎ ፡ በታ ላቅ ፡ ድምፅ ፡ ጮኸ ። ይህንም ፡ ብሎ ፡ አንቀ ላፋ ። ሳውልም ፡ በእርሱ ፡ መገደል ፡ ተስማ ምቶ ፡ ነበር ።

## የዓመፅ ሰውም የተባለው በሰይጣን ኃይልና ሥልጣን ይሰጠዋል

2 ተሰሎንቄ፡2÷1፣ 3-4 ፣ 8-9

ነገር ፡ ግን ÷ ወንድሞች ፡ ሆይ ÷ ስለ ፡ ጌታችን ፡ ስለ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ፡መምጣትና፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ስለ ፡ መሰብሰባችን ÷ ማንም ፡ በማናቸውም፡መንገድ፡ አያታላችሁ፤ ክህደቱ፡ አስቀድሞ ፡ ሳይመጣና ፡ የዓመፅ ፡ ሰው ፡ እርሱም ፡ የጥፋት ፡ ልጅ ፡ ሳይገለጥ ÷ አይደርስምና ። እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ነኝ፡ ብሎ፡ አዋጅ፡ እየነገረ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤተ ፡ መቅደስ፡ እስኪቀመጥ ፡ ድረስ ÷ አምላክ ፡ ከተባለው ፡ሁሉ ፡ ሰዎችም ፡ከሚያመልኩት፡ ሁሉ ፡ በላይ፡ ራሱን፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ የሚያደርገው ፡ ተቃዋሚ ፡ እርሱ ፡ ነው ። በዚያም፡ ጊዜ ፡ ጌታ፡ ኢየሱስ ፡ በአፉ፡ መንፈስ፡ የሚያጠፋው ÷ ሲመጣም፡ በመገለጡ፡ የሚሽረው ፡ ዓመፀኛ ፡ ይገለጣል ።

የዮሐንስ፡ ራእይ ፡13÷2 ፣ 7

ዘንዶውም ፡ ኃይሉንና ፡ ዙፋኑን ፡ ትልቅም ፡ ሥልጣን፡ ሰጠው ። በነገድና ፡ በወገንም ፡ በቋንቋም፡ በሕዝብም፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ሥልጣን፡ ተሰጠው ።

የዮሐንስ፡ ራእይ ፡13÷4

ለዘንዶውም፡ ሰገዱለት ÷ ለአውሬው ፡ ሥልጣን ፡ ሰጥቶታልና ፤ ለአውሬውም ፡ አውሬውን፡ ማን ፡ ይመስለዋል ÷ እርሱንስ ፡ ሊዋጋ፡ ማን ፡ ይችላል ? እያሉ ፡ ሰገዱለት ።

ዳንኤል ፡7 ÷ 25-26

በልዑሉም ፡ ላይ ፡ ቃልን ፡ ይናገራል ÷ የልዑ ልንም ፡ ቅዱሳን ፡ ይሰባብራል ÷ ዘመናትንና ፡ ሕግን ፡ ይለውጥ ፡ ዘንድ ፡ ያስባል ፡ እስከ ፡ ዘመ ንና ፡ እስከ ፡ ዘመናት ፡ እስከ ፡ እኩሌታ ፡ ዘመ ንም ፡ በእጁ ፡ ይሰጣሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ ፍርድ ፡ ይሆናል ÷ እስከ ፡ ፍጻሜም ፡ ድረስ ፡ ያፈርሱ ትና ፡ ያጠፉት ፡ ዘንድ ፡ ግዛቱን ፡ ያስወግዱታል ።

የዮሐንስ ፡ ራእይ 13÷5-9

በአርባ ፡ ሁለት ፡ ወርም ፡ እንዲ ሠራ ፡ ሥልጣን ፡ ተሰጠው ። እግዚአብሔር ንም ፡ ለመሳደብ ፡ ስሙንና ፡ ማደሪያውንም ፡ በሰማይም ፡ የሚያድሩትን ፡ ሊሳደብ ፡ አፉን ፡ ከፈተ ። ቅዱሳንንም ፡ ይዋጋ ፡ ዘንድ ፡ ድልም ፡ ያደርጋቸው ፡ ዘንድ ፡ ተሰጠው ፡ በነገድና ፡ በወ ገንም ፡ በቋንቋም ፡ በሕዝብም ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ሥል ጣን ፡ ተሰጠው ። ከዓለምም ፡ ፍጥረት ፡ ጀምሮ ፡ በታረደው ፡ በግ ፡ ሕይወት ፡ መጽሐፍ ፡ ስሞቻ ቸው ፡ ያልተጻፉ ፡ በምድር ፡ የሚኖሩ ፡ ሁሉ ፡ ይሰ ግዱለታል ። ጆሮ ፡ ያለው ፡ ቢኖር ፡ ይስማ ።

1 ጢሞቴዎስ ፡ 6÷12

መልካሙን ፡ የእምነት ፡ ገድል ፡ ተጋደል ፡ የተጠ ራህለትንም ፡ በብዙም ፡ ምስክሮች ፡ ፊት ፡ በመ ልካም ፡ መታመን ፡ የታመንህለትን ፡ የዘላለም ን ፡ ሕይወት ፡ ያዝ ።

## አንዳንድ የሃይማኖት መሪዎች የክርስቶስ ተቃዋሚ ዓለምን እንዲያታልል ያግዙታል

## ማምለክ ወይም መሞት !

የዮሐንስ፡ ራእይ፡13÷14-15፣19-20

በአውሬውም ፡ ፊት ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ ከተሰጡት ፡ ምልክቶች ፡ የተነሣ ፡ በምድር ፡ የሚኖሩትን ፡ ያስታል ፡ የሰይፍም ፡ ቍስል ፡ ለነበረውና ፡ በሕይወት ፡ ለኖረው ፡ ለአውሬው ፡ ምስልን ፡ እንዲያደርጉ ፡ በምድር ፡ የሚኖሩትን ፡ ይናገራል ። የአውሬው ፡ ምስል ፡ ሊናገር ፡ እንኳ ፡ ለአውሬውም ፡ ምስል ፡ የማይሰግዱለትን ፡ ሁሉ ፡ ሊያስገድላቸው ፡ ለአውሬው ፡ ምስል ፡ ትንፋሽ ፡ እንዲሰጠው ፡ ተሰጠው ። አውሬውም ፡ ተያዘ ፡ በእርሱም ፡ ፊት ፡ ተአምራትን ፡ እያደረገ ፡ የአውሬውን ፡ ምልክት ፡ የተቀበሉትን ፡ ለምስሉም ፡ የሰገዱትን ፡ ያሳተ ፡ ሐሰተኛው ፡ ነቢይ ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ተያዘ ፡ ሁለቱም ፡ በሕይወት ፡ ሳሉ ፡ በዲን ፡ ወደሚቃጠል ፡ ወደ ፡ እሳት ፡ ባሕር ፡ ተጣሉ ።

## የእግዚአብሔር ሰዎች ሌሎችአማልክትን አይቀበሉም

ዳንኤል፡3÷17-18

የምናመልከው ፡ አምላክ ችን ፡ ከሚነድደው ፡ ከእሳቱ ፡ እቶን ፡ ያድነን ፡ ዘንድ ፡ ይችላል ፡ ከእጅህም ፡ያድነናል ÷ ንጉሥ ፡ ሆይ ! ነገር ፡ ግን ÷ ንጉሥ ፡ ሆይ ÷ እርሱ ፡ ባያድነን ÷ አማልክትህን ፡ እንዳናመልክ ፡ ላቆምኸውም ፡ ለወርቁ ፡ ምስል ፡ እንዳንሰግድለት ፡ እወቅ ፡ አሉት ።

# የክርስቶስ ተቃዋሚ ለርሱ መ ገበር ወይም በራብ ማለቅ ነው

የዮሐንስ፡ ራእይ ፡13 ÷ 16-18

ታናናሾችና ፡ ታላላቆችም ፡ ባለ ፡ ጠጋዎችና ፡
ድሆችም ፡ ጌታዎችና ፡ ባሪያዎችም ፡ ሁሉ ፡
በቀኝ ፡ እጃቸው ፡ ወይም ፡ በግምባራቸው ፡
ምልክትን ፡ እንዲቀበሉ ÷ የአውሬውም ፡ ስ
ም ፡ ወይም ፡ የስሙ ፡ ቍጥር ፡ ያለው ፡ ምልክ
ት ፡ የሌለበት ፡ ማንም ፡ ሊገዛ ፡ ወይም ፡ ሊሸ
ጥ ፡ እንዳይችል ፡ ያደርጋል ። ጥበብ ፡ በዚህ ፡
አለ ። አእምሮ ፡ ያለው ፡ የአውሬውን ፡ ቍጥ
ር ፡ ይቍጠረው ፡ ቍጥሩ ፡ የሰው ፡ ቍጥር ፡ ነ
ውና ፡ ቍጥሩም ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ስድሳ ፡ ስድ
ስት ፡ ነው ።

## ለዳኑት የተሻለ ቀን እየመጣ ነው

የዮሐንስ፡ ራእይ ፡7 ÷ 14-17

እነዚህ ፡ ከታላቁ ፡ መከራ ፡ የመጡ ፡
ናቸው ፡ ልብሳቸውንም ፡ አጥበው ፡ በበጉ ፡
ደም ፡ አነጹ ። ስለዚህ ፡ በእግዚአብሔር ፡
ዙፋን ፡ ፊት ፡ አሉ ÷ ሌሊትና ፡ ቀንም ፡ በመቅ
ደሱ ፡ ያመልኩታል ፡ በዙፋኑም ፡ ላይ ፡ የተቀ
መጠው ፡ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ ያድርባቸዋል ። ከእ
ንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አይራቡም ፡ ከእንግዲህም ፡
ወዲህ ፡ አይጠሙም ፡ ፀሐይም ፡ ትኩሳትም ፡
ሁሉ ፡ ከቶ ፡ አይወርድባቸውም ፡ በዙፋኑ ፡
መካከል ፡ ያለው ፡ በጉ ፡ እረኛቸው ፡ ይሆናልና ፡
ወደ ፡ ሕይወትም ፡ ውኃ ፡ ምንጭ ፡ ይመራቸዋ
ልና ፡ እግዚአብሔርም ፡ እንባዎችን ፡ ሁሉ ፡
ከዓይናቸው ፡ ያብሳል ።

## በሞላ ሆድ ገሃነም ከመግባት በጾ ሆድ ሆኖ መንግሥተ ሰማያት መግባት ይሻላል !

# ለመግዛትና ለመሸጥ ሲሉ የክርስቶስ ተቃዋሚውን ምልክት በሰውነታቸው ላይ የተቀበሉ ሰዎች ሁሉ የተኰነኑ ናቸው

የዮሐንስ፡ ራእይ ፡14 ÷ 9-13

ሦስተኛም፡መልአክ፡ተከተላቸው ÷ በታላቅ፡ ድምፅ ፡ እንዲህ ፡ እያለ ፡— ለአውሬውና ፡ ለምስሉ ፡የሚሰግድ ፡በግምባሩም ፡ ወይም፡ በእጁ፡ ምልክቱን፡ የሚቀበል ፡ ማንም ፡ ቢኖር ÷ እርሱ፡ ደግሞ ፡ በቍጣው ፡ ጽዋ ፡ ሳይቀላቅል ፡ ከተዘጋጀው ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ቍጣ ፡ ወይን ፡ ጠጅ፡ ይጠጣል ፡ በቅዱሳንም ፡ መላእክትና ፡ በበጉ ፡ ፊት ፡ በእሳትና ፡ በዲን ፡ ይሣቀያል ። የሥቃያቸውም ፡ ጢስ ፡ ለዘላለም ፡ እስከ ፡ ዘላለም ፡ ድረስ፡ ይወጣል ÷ ለአውሬውና ፡ ለምስሉም ፡ የሚሰግዱ ፡ የስሙንም ፡ ምልክት ፡ የሚቀበል ፡ ሁሉ፡ ቀንና ፡ ሌሊት ፡ ዕረፍት ፡ የላቸውም ።

የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዛት ፡ የሚጠብቁት ፡ ኢየሱስንም ፡ በማመን ፡ የሚጸኑት ፡ ቅዱሳን ፡ ትዕግሥታቸው ፡ በዚህ ፡ ነው ።

ከሰማይም ፡— ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ በጌታ ፡ የሚሞቱ ፡ ሙታን ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው ። መንፈስ ፡— አዎን ÷ ከድካማቸው ፡ ያርፉ ፡ ዘንድ ÷ ሥራቸውም ፡ ይከተላቸዋል ፡ ይላል ፡ ብለህ ፡ ጻፍ ፡ የሚል ፡ ድምፅ ፡ ሰማሁ ።

# የእግዚአብሔር ቁጣ ወደ ም ድር ከመምጣቱ በፊት የሰይ ጣን ምልክትና ምስሉ ድል ሆኑ

የዮሐንስ፡ ራእይ፡15÷1-3 ፣ 16÷1

ሰባት ፡ መቅሠፍቶች ፡ የያዙ ፡ ሰባት ፡ መላእክት ፡ታዩ ።

በእሳትም ፡ የተቀላቀለውን ፡ የብርጭቆ ፡ ባሕር፡ የሚመስለውን፡ አየሁ ÷ በአውሬውና፡ በምስሉም፡ በስሙም፡ቊጥር፡ ላይ፡ ድል፡ ነሥተው ፡ የነበሩት ፡ የእግዚአብሔርን ፡ በገና ፡ ይዘው ፡ በብርጭቆ ፡ ባሕር ፡ ላይ ፡ ሲቆሙ ፡ አየሁ ።

ሁሉን፡የምትገዛ፡ ጌታ ፡ አምላክ ፡ ሆይ ÷ ሥራህ ፡ ታላቅና፡ ድንቅ፡ነው ፡ የአሕዛብ ፡ ንጉሥ፡ ሆይ ÷ መንገድህ ፡ ጻድቅና ፡ እውነተኛ ፡ ነው ፡ እያሉ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ባሪያ ፡ የሙሴን ፡ ቅኔና ፡ የበጉን፡ቅኔ፡ ይዘፃ ራሉ ።

ለሰባቱም ፡ መላእክት ፡— ሄዳችሁ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቊጣ፡ ጽዋዎች ፡ በምድር ፡ ውስጥ፡ አፍስሱ ፡ የሚል ፡ ታላቅ ፡ ድምፅ ፡ ከመቅደሱ ፡ ሰማሁ ።

## ራሳቸውን የተቆረጡት ስማዕታት ነገሡ

የዮሐንስ፡ ራእይ፡ 20 ÷ 4

ስለ ፡ ኢየሱስም ፡ ምስክርና ፡ ስለ ፡እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ራሶቻቸው ፡ የተቈረጡባቸውን ፡ ሰዎች ፡ ነፍሳት ÷ ለአውሬውና ፡ ለምስሉም ፡ያልሰገዱትን ፡ ምልክቱንም ፡ በግምባራቸው ፡በእጆቻቸውም፡ ላይ ፡ ያልተቀበሉትን ፡ አየሁ ፡ ከክርስቶስም ፡ ጋር ፡ ሺህ ፡ ዓመት ፡ ኖሩና ፡ ነገሡ ።

## ሕዝብ እንዲተላለቁ አጋ ንንት ይሰበስባቸዋል

የዮሐንስ ፡ ራእይ ፡16÷14-16

ምልክት ፣ እያደረጉ ፡ የአጋንንት ፣ መናፍስት ፣ ናቸውና ÷ በታላቁም ፡ ሁሉን ፣ በሚገዛ ፣ በእ ግዚአብሔር ፣ ቀን ፣ ወደሚሆነው ፣ ጦር ፣ እንዲ ያስከትቱአቸው ፣ ወደ ፣ ዓለም ፣ ሁሉ ፣ ነገሥታ ት ፣ ይወጣሉ ። በዕብራይስጥም ፣ አርማጌዶን፣ ወደሚባል ፣ ስፍራ ፣ አስከተቱአቸው ።

## ክርስቶስ ምድሩንና ለራሱ የ መረጣቸውን የእስራኤል ሕ ዝብ ነፃ ያወጣቸዋል

ዘካርያስ ፡12÷2-3 ፣14÷3 ፣12

እነሆ ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ በዙሪያዋ ፡ ላሉት፣ ለአሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ የመንገድገድ ፡ ዋንጫ ፡ አ ደርጋታለሁ ፡ በዚያም ፡ ቀን ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ ለአሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ ከባድ ፡ ድንጋይ ፡ አደርጋታለ ሁ ፡ የሚሸከሙአት ፡ ሁሉ ፡ እጅግ ፡ ይቈስላሉ ፣ የምድርም ፡ አሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ በላይዋ ፡ ላይ ፣ ይ ከማቻሉ ።

እግዚአብሔርም ፡ ይወጣል ÷ በሰልፍም ቀን ፣ እንደ ፡ ተዋጋ ፡ ከእነዚያ ፡ አሕዛብ ፡ ጋር ይዋጋል ።

እግዚአብሔርም ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ጋር ፡ የተ ዋጉትን ፡ አሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ የሚቀሥፍበት ፡ ቸ ፈር ፡ ይህ ፡ ነው ፡ በእግራቸው ፡ ሲቆሙ ፡ ሥጋ ቸው ፡ ይበሰብሳል ÷ ዓይኖቻቸውም ፣ በዓይኑ ፡ ስባቸው ፡ ውስጥ ፡ ይበሰብሳሉ ÷ ምላሳቸውም፣ በአፉቸው ፡ ውስጥ ፡ ይበሰብሳል ።

ሮሜ ፡ 1÷18

እውነትን ፡ በዓመፃ ፡ በሚከለክሉ ፡ ሰዎች ፡ በኃጢአተኝነታቸውና ፡ በዓመፃቸው ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቍጣ ፡ ከሰማይ ፡ ይገለጣልና ።

የዮሐንስ ፡ ራእይ ፡ 19÷15፣16

አሕዛብንም ፡ ይመታበት ፡ ዘንድ ፡ ስለታም ፡ ሰይፍ ፡ ከአፉ ፡ ይወጣል ፡ እርሱም ፡ በብረት ፡ በትር ፡ ይገዛቸዋል ፡ እርሱም ፡ ሁሉን ፡ የሚገዛ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ የብርቱ ፡ ቍጣውን ፡ ወይን ፡ መጥመቂያ ፡ ይረግጣል ። በልብሱና ፡ በጭኑም ፡ የተጻፈበት ፡ የነገሥታት ፡ ንጉሥና ፡ የጌታዎች ፡ ጌታ ፡ የሚል ፡ ስም ፡ አለው ።

የዮሐንስ ፡ ራእይ ፡ 20÷6

ዳሩ ፡ ግን ፡ የእግዚአብሔርና ፡ የክርስቶስ ፡ ካህናት ፡ ይሆናሉ ፡ ከእርሱም ፡ ጋር ፡ ይህን ፡ ሺህ ፡ ዓመት ፡ ይነግሣሉ ።

ዳንኤል ፡ 2÷44

በእነዚያም ፡ ነገሥታት ፡ ዘመን ፡ የሰማይ ፡ አምላክ ፡ ለዘላለም ፡ የማይፈርስ ፡ መንግሥት ፡ ያስነሣል ፡ ለሌላ ሕዝብም ፡ የማይሰጥ ፡ መንግሥት ፡ ይሆናል ።

## የዓለም ሕዝብ ሁሉ ጌታ ክርስቶስን ያመልካሉ !

መዝሙረ ፡ ዳዊት ፡ 86 ÷ 9

ያደረግሃቸው ፡ አሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ ይመጣሉ ÷ አቤቱ ÷ በፊትህም ፡ ይሰግዳሉ ÷ ስምህንም ፡ ያከብራሉ ።

የዮሐንስ፡ ራእይ:12÷7-10

በሰማይም ፥ ሰልፍ ፥ ሆነ ፤ ሚካኤልና ፥ መላእክቱ ፥ ዘንዶውን፥ ተዋጉ ። ዘንዶውም ፥ ከመላእክቱ ፥ ጋር፥ ተዋጋ ፡ አልቻላቸውምም ÷ ከዚያም ፥ ወዲያ ፥ በሰማይ ፥ ስፍራ ፥ አልተገኘላቸውም ። ዓለሙንም ፥ ሁሉ ፥ የሚያስተው ÷ ዲያብሎስና ፥ ሰይጣን፥ የሚባለው ፥ ታላቁ ፥ ዘንዶ ፥ እርሱም ፥ የቀደመው ፥ እባብ ፥ ተጣለ ፤ ወደ ፥ ምድር ፥ ተጣለ ፥ መላእክቱም ፥ ከእርሱ ፥ ጋር፥ ተጣሉ ። ታላቅም ፥ ድምፅ ፥ በሰማይ ፥ ሰማሁ ፥ እንዲህ ፥ ሲል ፥—

አሁን ፥ የአምላካችን ፡ ማዳንና ፥ ኃይል ፥ መንግሥትም ፥ የክርስቶስም ፥ ሥልጣን ፥ ሆነ÷ቀንና ፥ ሌሊትም፥ በአምላክችን ፥ ፊት ፥ የሚከሳቸው ፥ የወንድሞቻችን ፥ ከሳሽ ፥ ተጥሎአልና ።

# የዚህ ጦርነት መሳሪያዎች

የዮሐንስ፡ ራእይ:12÷11

እነርሱም ፥ ከበጉ ፥ ደም ፥ የተነሣ፥ ከምስክራቸውም ፥ ቃል ፥ የተነሣ ፥ ድል ፥ነሡት ÷ ነፍሳቸውንም ፥ እስከ ፥ ሞት፥ ድረስ ፥ አልወደዱም ።

# የሰይጣን የዘለዓለም ጥፋት

የዮሐንስ፡ ራእይ:20÷9-10

እሳትም ፥ ከሰማይ ፡ ከእግዚአብሔር ፥ ዘንድ ፥ ወርዳ ፥ በላቻቸው ። ያሳታቸውም ፥ ዲያብሎስ ፥ አውሬውና ፥ ሐሰተኛው ፡ ነቢይ ፥ ወዳሉበት ፥ ወደ ፥ እሳቱና ፥ ወደ ፡ ዲኑ ፥ ባሕር ፥ ተጣለ ፤ ለዘላለምም ፥ እስከ ፥ ዘላለም ፡ ቀንና ፥ ሌሊት ፥ ይሣቀያሉ ።

## ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለዘለ ዓለም ይነግሣል

1 ዜና ፡ መዋዕል ፡ 29 ÷ 11

አቤቱ ÷ በሰማይና ፡ በምድር ፡ ያለው ፡ ሁሉ ፡ የአንተ ፡ ነውና ፡ ታላቅነትና ፡ ኃይል ÷ ክብርም ÷ ድልና ፡ ግርማ ፡ ለአንተ ፡ ነው ፤ አቤቱ ÷ መን ግሥት ፡ የአንተ ፡ ነው ÷ አንተም ፡ በሁሉ ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያልህ ፡ ራስ ፡ ነህ ።

1 ቆሮንቶስ ፡ 15 ÷ 22-26

ሁሉ ፡ በአዳም ፡ እንደሚሞቱ ፡ እንዲሁ ፡ ሁሉ ፡ በክርስቶስ ፡ ደግሞ ፡ ሕያዋን ፡ ይሆናሉና ። ነገር ፡ ግን ፡ እያ ንዳንዱ ፡ በራሱ ፡ ተራ ፡ ይሆናል ፤ ክርስቶስ ፡ እንደ ፡ በኵራት ፡ ነው ÷ በኋላም ፡ በመምጣቱ ፡ ለክርስቶስ ፡ የሆኑት ፡ ናቸው ፤ በኋላም ÷ መንግ ሥቱን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ለአባቱ ፡ አሳልፎ ፡ በሰጠ ፡ ጊዜ ፡ አለቅነትንም ፡ ሁሉና ፡ ሥልጣንን ፡ ሁሉ ፡ ኃይልንም ፡ በሻረ ፡ ጊዜ ፡ ፍጻሜ ፡ ይሆ ናል ። ጠላቶቹን ፡ ሁሉ ፡ ከእግሩ ፡ በታች ፡ እስ ኪያደርግ ፡ ድረስ ፡ ሊነግሥ ፡ ይገባዋልና ። የኋ ኛው ፡ ጠላት ፡ የሚሻረው ፡ ሞት ፡ ነው ።

የዮሐንስ ፡ ራእይ ፡ 11 ÷ 15

ሰባተኛውም ፡ መልአክ ፡ ነፋ ፤ በሰማይም ፡ የዓለም ፡ መንግሥት ፡ ለጌታችንና ፡ ለእ ርሱ ፡ ለክርስቶስ ፡ ሆነች ÷ ለዘላለምም ፡ እስከ ፡ ዘላለም ፡ ይነግሣል ፡ የሚሉ ፡ ታላላቅ ፡ ድምፆች ፡ ሆኑ ።

# ጠላቶችህ ሰይጣንና ዲያ ብሎስ ናቸው

## ሰይጣን ሰውነትንና ነፍስን በ ግብረ ሰዶም ተግባርና ሕፃን ን በማስወረድ ነፍሰገዳይነት እንዲሁም በሰይጣን በመያዝ በሽታ ያረክሰዋል

ሮሜ ፡1÷27

ወንዶችም ፡ በወንዶች ፡ነውር ፡ አድርገው ፡ በስሕተታቸው ፡ የሚገባውን ፡ ብድራት ፡ በ ራሳቸው ፡ ተቀበሉ ።

ም ሳ ሌ፡ 6÷16-17

እግዚአብሔር ፡ የሚጠላቸው ፡ ስድስት ፡ ኑ ሮች ፡ ናቸው ÷

ሰባትንም ፡ ነፍሱ ፡ አጥብቃ ፡ ትጸየፈዋለች ፡ ትዕቢተኛ ፡ ዓይን ፡ ሐሰተኛ ፡ ምላስ ÷ ንጹሕን ፡ ደም ፡ የምታፈስስ ፡ እጅ ÷

ማቴዎስ ፡12÷45

ከዚያ ፡ ወዲያ ፡ ይሄድና ፡ ከእርሱ ፡ የከፉ ትን ፡ ሰባት ፡ ሌሎችን ፡ አጋንንት ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ይወስዳል ፡ ገብተውም ፡ በዚያ ፡ ይኖራሉ ፡ ለዚ ያም ፡ ሰው ፡ ከፊተኛው ፡ ይልቅ ፡ የኋለኛው ፡ ይብስበታል ።

# በክርስቶስ ደምና ማንነት አማ ካይነት ከሚገኘው ይቅርታ ፤ ንጽሕናና ደኅንነት በስተቀር በሌላ የሚመራ ትምህርት አሳ ችና ተሳሳች ነው

ማቴዎስ ፡ 24÷ 4-5 ፣ 11

ኢየሱስም ፡ መልሶ ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፡ ማንም ፡ እንዳያስታችሁ ፡ ተጠንቀቁ ። ብዙ ዎች ፡ – እኔ ፡ ክርስቶስ ፡ ነኝ ፡ እያሉ ፡ በስሜ ፡ ይመጣሉና ፡ ብዙዎችንም ፡ ያስታሉ ።

ብዙ ፡ ሐሰተኞች ፡ ነቢያትም ፡ ይነሣሉ ፡ ብ ዙዎችንም ፡ ያስታሉ ።

# ይቅር በልና ይቅርታ ተቀበል

ማቴዎስ ፡ 6 ÷14

ለሰዎች ፡ ኃጢአታቸውን ፡ ይቅር ፡ ብትሉ የሰማዩ ፡ አባታችሁ ፡ እናንተን ፡ ደግሞ ፡ ይቅር ፡ ይላችኋልና ።

# በክቡር የክርስቶስ ደም መዳን

1 ጴጥሮስ ፡ 1 ÷18-19 ፣ 21

ከአባቶቻችሁ ፡ ከወረሳችሁት ፡ ከከንቱ ፡ ኑሮአችሁ ፡ በሚያልፍ ፡ ነገር ፡ በብር ፡ ወይም ፡ በወርቅ ፡ ሳይሆን ÷ ነውርና ፡ እድፍ ፡ እንደ ፡ ሌለው ፡ እንደ ፡ በግ ፡ ደም ፡ በክቡር ፡ የክርስ ቶስ ፡ ደም ፡ እንደ ፡ ተዋጃችሁ ፡ ታውቃላችሁ ። በእግዚአብሔር ፡ በእርሱ ፡ ስለምታምኑ ።

## ኃጢአት ይሠለጥንበታል

ኢሳይያስ ፡ 64 ÷ 6

ሁላችን ፡ እንደ ፡ ርኩስ በው ፡ ሆነናል ፡ ጽድቃችንም ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ መርገም ፡ ጨርቅ ፡ ነው ፡ ሁላችንም ፡ እንደ ፡ ቅጠል ፡ ረግፈናል ፡ በደላችንም ፡ እንደ ፡ ነፋስ ፡ ወስዶናል ።

ኤፌሶን ፡ 2 ÷ 2-3

በእነርሱም ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ እን ዳለው ፡ ኑሮ ÷ በማይታዘዙትም ፡ ልጆች ፡ ላይ አሁን ፡ ለሚሠራው ፡ መንፈስ ፡ አለቃ ፡ እንደ ፡ ሆነው ፡ በአየር ፡ ላይ ፡ ሥልጣን ፡ እንዳለው ፡ አለቃ ፡ ፈቃድ ÷ በፊት ፡ ተመላለሳችሁባቸው ። በእነዚህም ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ እኛ ፡ ሁላችን ፡ ደግሞ ÷ የሥጋችንንና ፡ የልቡናችንን ፡ ፈቃድ ፡ እያደረግን ÷ በሥጋችን ፡ ምኞት ፡ በፊት ፡ እን ኖር ፡ ነበርን ፡ እንደ ፡ ሌሎቹም ፡ ደግሞ ፡ ከፍጥረ ታችን ፡ የቍጣ ፡ ልጆች ፡ ነበርን ።

2 ቆሮንቶስ ፡ 4 ÷ 3-4

ወንጌላችን ፡ የተከደነ ፡ ቢሆን ፡ እንኳ ፡ የተ ከደነባቸው ፡ ለሚጠፉ ፡ ነው ። ለእነርሱም ፡ የእ ግዚአብሔር ፡ ምሳሌ ፡ የሆነ ፡ የክርስቶስ ፡ የክ ብሩ ፡ ወንጌል ፡ ብርሃን ፡ እንዳያበራላቸው ፡ የ ዚህ ፡ ዓለም ፡ አምላክ ፡ የማያምኑትን ፡ አሳብ ፡ አሳወረ ።

## ድል አድራጊነት በክርስቶስ ነው

ሮሜ ፡ 3÷1 ፣ 4

እንግዲህ ፡ በክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ ላሉት ፡ አሁን ፡ ኩነኔ ፡ የለባቸውም ። እንደ ፡ መንፈስ ፡ ፈቃድ ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ ሥጋ ፡ ፈቃድ ፡ በማን መላለስ ።

ማቴዎስ ፡ 13 ÷ 38

እርሻውም ፡ ዓለም ፡ ነው ፡ መልካ ሙም ፡ ዘር ፡ የመንግሥት ፡ ልጆች ፡ ናቸው ፡ እንክርዳዱም ፡ የክፉው ፡ ልጆች ፡ ናቸው ።

እናንተ ፡ ከአባታችሁ ፡ ከዲያብሎስ ፡ ናች ሁ ፡ የአባታችሁንም ፡ ምኞት ፡ ልታደርጉ ፡ ትወ ዳላችሁ ። —ዮሐንስ ፡ 8 ÷ 44

ማቴዎስ ፡ 12 ÷ 30

ከእኔ ፡ ጋር ፡ ያልሆነ ፡ ይቃወመኛል ፡ ከእኔ ፡ ጋርም ፡ የማያከማች ፡ ይበትናል ።

## በዚህ ምክንያት ከክርስቶስ መንፈስ አዲስ መወለድ አለብን

2 ቆሮንቶስ ፡ 5 ÷ 17

ስለዚህ ፡ ማንም ፡ በክርስቶስ ፡ ቢሆን ፡ አዲስ ፡ ፍጥረት ፡ ነው ፡ አሮጌው ፡ ነገር ፡ አልፎአል ፡ እነሆ ፡ ሁሉም ፡ አዲስ ፡ ሆኖአል ።

ዮሐንስ ፡ 10 ÷ 27-28

በጎቼ ፡ ድምፄን ፡ ይሰማሉ ፡ እኔም ፡ አውቃቸዋ ለሁ ፡ ይከተሉኝማል ፡ እኔም ፡ የዘላለም ፡ ሕይ ወትን ፡ እሰጣቸዋለሁ ።

## አሁኑኑ ራስህን ለጌታ ኢየሱስ አስረክብ

2 ቆሮንቶስ ፡ 6 ÷ 2

እነሆ ፡ የተወደደው ፡ ሰዓት ፡ አሁን ፡ ነው ፡ እነሆ ፡ የመዳን ፡ ቀን ፡ አሁን ፡ ነው ።

1 ዮሐንስ ፡ 1 ÷ 9

በኃጢአታችን ፡ ብንናዘዝ ፡ ኃጢአታችን ን ፡ ይቅር ፡ ሊለን ፡ ከዓመፃም ፡ ሁሉ ፡ ሊያነጻን ፡ የታመነና ፡ ጻድቅ ፡ ነው ።

ሮሜ ፡ 8÷35 ፣ 37

ከክርስቶስ ፡ ፍቅር ፡ ማን ፡ ይለየናል ? መከራ ፥ ወይስ ፡ ጭንቀት ፥ ወይስ ፡ ስደት ፥ ወይስ ፡ ራብ ፥ ወይስ ፡ ራቁትነት ፥ ወይስ ፡ ፍርሃት ፥ ወይስ ፡ ሰይፍ ፡ ነውን ?

በዚህ ፡ ሁሉ ፡ ግን ፡ በወደደን ፡ በእርሱ ፡ ከአሸናፊዎች ፡ እንበልጣለን ።

1 ዮሐንስ ፡ 5÷4

ከእግዚአብሔር ፡ የተወለደ ፡ ሁሉ ፡ ዓለምን፡ ያሸንፋልና ፡ ዓለምንም ፡ የሚያሸንፈው ፡ እምነታችን ፡ ነው ።

የዮሐንስ ፡ ራእይ ፡ 2÷17

መንፈስ ፡ ለአብያተ ፡ ክርስ ቲያናት ፡ የሚለውን ፡ ጆሮ ፡ ያለው ፡ ይስማ ። ድል ፡ ለነሣው ፡ ከተሰወረ ፡ መና ፡ እሰጠዋለሁ ፥ ነጭ ፡ ድንጋይንም ፡ እሰጠዋለሁ ፥ በድንጋዩም ፡ ላይ ፡ ከተቀበለው ፡ በቀር ፡ አንድ ፡ ስንኳ ፡ የሚያውቀው ፡ የሌለ ፡ አዲስ ፡ ስም ፡ ተጽፎአል ።

የዮሐንስ ፡ ራእይ ፡ 2÷26

ድል ፡ ለነሣውና ፡ እስከ ፡ መጨረሻም ፡ ሥራዬን ፡ ለጠበቀው ፡ እኔ ፡ ደግሞ ፡ ከአባቴ ፡ እንደ ፡ ተቀበልሁ ፡ በአሕዛብ ፡ ላይ ፡ ሥልጣንን ፡ እሰጠዋለሁ ፤

**አንተ በእግዚአብሔር ዘንድ በጣም ተፈላጊ ነህ ። ይኸንንም ጎልጎታ ያረጋግጥልናል ! እግዚአብሔር ደግሞ ለአንተ በጣም ያስፈልግሃል !**

ብቃታችን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ነው ፡ እንጂ ፥ በገዛ ፡ እኛችን ፡ እንደሚሆን ፡ አንዳችን ፡ እንኳ ፡ ልናስብ ፡ ራሳችን ፡ የበቃን ፡ አይደለንም ። — 2 ቆሮንቶስ ፡ 3÷5

## የመረጡት ከክርስቶስ ጋር በ ክብር ይገለጣሉ

ቈላስይስ ፡ 3 ፥ 1-2 ፣ 4-6

እንግዲህ ፡ ከክርስቶስ ፡ ጋር ፡ ከተነሣችሁ ፥ ክርስቶስ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቀኝ ፡ ተቀምጦ ፡ ባለበት ፡ በላይ ፡ ያለውን ፡ እሹ ፡ በላይ ፡ ያለውን ፡ አስቡ ፡ እንጂ ፡ በምድር ፡ ያለውን ፡ አይደለም ።

ሕይወታችሁ ፡ የሆነ ፡ ክርስቶስ ፡ በሚገለጥበት ፡ ጊዜ ፥ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ እናንተ ፡ ደግሞ ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ በክብር ፡ ትገለጣላችሁ ።

እንግዲህ ፡ በምድር ፡ ያሉቱን ፡ ብልቶቻችሁን ፡ ግደሉ ፥ እነዚህም ፡ ዝሙትና ፡ ርኵሰት ፡ ፍትወትም ፡ ክፉ ፡ ምኞትም ፡ ጣዖትንም ፡ ማምለክ ፡ የሆነ ፡ መጐምጀት ፡ ነው ፡ በእነዚህም ፡ ጠንቅ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቍጣ ፡ በማይታዘዙ ፡ ልጆች ፡ ላይ ፡ ይመጣል ።

## ያልመረጡት ከሰይጣን ጋር ይረገማሉ

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ በግራው ፡ ያሉትን ፡ ደግሞ ፡ ይላቸዋል ፡ እናንተ ፡ ርጉማን ፡ ለሰይጣንና ፡ ለመላእክቱ ፡ ወደ ፡ ተዘጋጀ ፡ ወደ ፡ ዘላለም ፡ እሳት ፡ ከእኔ ፡ ሂዱ ። —ማቴዎስ ፡ 25 ፥ 41

መዝሙረ ፡ ዳዊት ፡ 9 ፥ 17

ኃጢአተኞች ፡ ወደ ፡ ሲኦል ፡ ይመለሳሉ ፥ እግዚአብሔርን ፡ የሚረሱ ፡ አሕዛብም ፡ ሁሉ ።

ማርቆስ ፡ 9 ፥ 43

እጅህ ፡ ብታሰናክልህ ፡ ቍረጣት ፡ ሁለት ፡ እጅ ፡ ኖሮህ ፡ ትላቸው ፡ ወደማይሞትበት ፡ እሳቱም ፡ ወደማይጠፋበት ፡ ወደ ፡ ገሃነም ፡ ወደማይጠፋ ፡ እሳት ፡ ከመሄድ ፡ ጕንድሽ ፡ ሆነህ ፡ ወደ ፡ ሕይወት ፡ መግባት ፡ ይሻላል ።

## ራስህን ዝቅ ዝቅ አድርግ

ማቴዎስ ፡ 18 ÷ 2 - 4

ኢየሱስ ፡ – ሕፃንም ፡ ጠርቶ ፡ በመካከላቸው ፡ አቆመ ፡ እንዲህም ፡ አለ ፡ እውነት ፡ እላችኋለሁ ፡ ከልተመለሳችሁ ፡ እንደ ፡ ሕፃናትም ፡ ካልሆናችሁ ፡ ወደ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ከቶ ፡ አትገቡም ። እንግዲህ ፡ እንደዚህ ፡ ሕፃን ፡ ራሱን ፡ የሚያዋርድ ፡ ሁሉ ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ የሚበልጥ ፡ እርሱ ፡ ነው ።

## ኃጢአትን ተናዘዝ

ማርቆስ ፡ 1 ÷ 4 ፣ 14-15

ዮሐንስ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ እያጠመቀ ፡ የንስሐንም ፡ ጥምቀት ፡ ለኃጢአት ፡ስርየት ፡ እየሰበከ ፡ መጣ ።

ዮሐንስም ፡ አልፎ ፡ ከተሰጠ ፡ በኋላ ፡ ኢየሱስ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መንግሥት ፡ ወንጌል ፡ እየሰበከና ፡ – ዘመኑ ፡ ተፈጸመ ፡ የእግዚአብሔርም ፡ መንግሥት ፡ ቀርባለች ፡ ንስሐ ፡ ግቡ ፡ በወንጌልም ፡ እመኑ ፡ እያለ ፡ ወደ ፡ ገሊላ ፡ መጣ ።

ሉቃስ ፡ 13 ÷ 3

እላችኋለሁ ÷ አይደለም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ንስሐ ፡ ባትገቡ ፡ ሁላችሁ ፡ እንዲሁ ፡ ትጠፋላችሁ።

የሐዋርያት ፡ ሥራ ፡ 3 ÷ 19

እንግዲህ ፡ ከጌታ ፡ ፊት ፡ የመጽናናት ፡ ዘመን ፡ እንድትመጣላችሁ ፡ አስቀድሞም ፡ ለእናንተ ፡ የመረጠውን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ እንዲልክላችሁ ÷ ኃጢአታችሁ ፡ ይደመሰስ ፡ ዘንድ ፡ ንስሐ ፡ ግቡ ፡ ተመለሱም ።

# ዛሬውኑ ክርስቶስን እንደ አ ዳኝህ አድርገህ ተቀበለው !

## ራስህን ለኢየሱስ ክርስቶስ ስጥ

መዝሙረ ፡ ዳዊት ፡ 37÷5

መንገድህን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አደራ ፡ ስጥ ÷ በእርሱም ፡ ታመን ÷ እርሱም ፡ ያደርግልሃል ።

ዮሐንስ ፡ 3÷16

በእርሱ ፡ የሚያምን ፡ ሁሉ ፡ የዘላለም ፡ ሕይ ወት ፡ እንዲኖረው ፡ እንጂ ፡ እንዳይ ጠፋ ፡ እግ ዚአብሔር ፡ አንድያ ፡ ልጁን ፡ እስኪሰጥ ፡ ድረስ ፡ ዓለሙን ፡ እንዲሁ ፡ ወዶአልና ።

የሐዋርያት ፡ ሥራ ፡16÷31

እነርሱም ፡ በጌታ ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እመን ፡ አንተና ፡ቤተ ፡ ሰዎችህም ፡ ትድናላችሁ ፡ አሉት ።

# ዛሬውኑ ክርስቶስን እንደ አ ዳኝህ አድርገህ ተቀበለው !

## እግዚአብሔር የእርሱ ልጆች የመሆንን ሥልጣን ይሰጠናል

ዮሐንስ ፡1÷12፤14÷27

ለተቀበሉት ፡ ሁሉ ፡ ግን ፥ በስሙ ፡ ለሚያምኑት ፡ ለእነርሱ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጆች ፡ ይሆኑ ፡ ዘንድ ፡ ሥልጣንን ፡ ሰጣቸው ፡

ሰላምን ፡ እተውላችኋለሁ ፥ ሰላሜን ፡ እሰጣችኋለሁ ።

## ክርስቶስ አዳኝህ እንደ ሆነ በግልጽ መስክር

ሮሜ ፡10÷9-11

ኢየሱስ ፡ ጌታ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በአፍህ ፡ ብትመሰክር ፡ እግዚአብሔርም ፡ ከሙታን ፡ እንዳነሣው ፡ በልብህ ፡ ብታምን ፡ ትድናለህና ፤ ሰው ፡ በልቡ ፡ አምኖ ፡ ይጸድቃልና ፡ በአፉም ፡ መስክሮ ፡ ይድናልና ። መጽሐፍ ፡— በእርሱ ፡ የሚያምን ፡ ሁሉ ፡ አያፍርም ፡ ይላልና ።

Published in numerous languages as God supplies funds in answer to prayer. If you would like more copies for prayerful distribution, write in English. Specify which language(s) you need and how many booklets.
**World Missionary Press, PO Box 120, New Paris, IN 46553-0120 USA**

Read booklets online or by App
www.wmp-readonline.org

www.wmpress.org

1-18

1411 Amharic SVC